**ረኀቡና ኢሕአዴጋዊ እውነታዎች**
ኤርሚያስ ለገሰ



በገፅ 6

**እድገቱ ለማን ነው? አዲስ ትርጉም የሚያስፈልገው የልማት መርህ**
አክሎግ ቢራራ (ዶ/ር)



በገፅ 6

**"በአውሮፓ አይሁድ በተገኘበት ሲገደል ግብጽ ውስጥ ሚኒስትር ሆኖ ይሾም ነበር"**
አምባሳደር አቡባከር ኸፍኒ ማህሙድ



በገፅ 5

# የቀለም ቀንድ

ቅጽ 3 ቁጥር 19 ህዳር 21 ቀን 2008ዓ.ም ዋጋው ብር 10.00




## ብሔርን መሠረት ያደረገው የዜጎች መፈናቀል ተባብሷል

**•ጥቃቱ የሚቀነባበረውና የሚመራው በመንግሥት ሹመኞች ነው ተብሏል**

የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) ሕዳር 16 ቀን 2008 ዓ.ም. በሰጠው ይፋ ጋዜጣዊ መግለጫ ብሔርን መሠረት ያደረጉና በልማት ስም የሚፈናቀሉ ዜጎች ጉዳይ እንዳሳሰበው ገለጸ። ሰመጉ ጋዜጠኞች፣ የውጭ ዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ አባላትና የሚመለከታው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ተወካዮች በተገኙበት ባደረገው መግለጫ ከዚህ በፊት በነሐሴ ወር 2007 ዓ.ም. በ136ኛ 138ኛ ልዩ መግለጫዎቹ ዜጎቹ የሚገኙበትን አሳሳቢ ሁኔታ የገለጸ ሲሆን እስካሁን ድረስ በመሻሻል ፈንታ ተባብሰው በመቀጠላቸው ይህን ጋዜጣው መግለጫ ለማውጣት ተገድጃለሁ ብሏል።

በምዕራብ ሸዋ ዞን ኖኖ ወረዳ ከባለፈው ሚያዚያ ወር ጀምሮ በወረዳው የመንግሥት ባለስልጣናት የአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል ተብሏል። ንብረትነታቸው የአማራ የሆኑ ከ125 በላይ የሳርና የቆርቆሮ ቤቶች ተዘርፈው ሙሉ በሙሉ የወደሙ ሲሆን የሞትና የአካል ጉዳትም ሰለባ ሆነዋል። እንደ ሰመጉ 136 ልዩና ጋዜጣዊ መግለጫ ከሆነ ግድያውንና ማፈናቀሉን የመሩትና ያከናወኑት የኖኖ ወረዳ በተለያየ እርከን ላይ የሚገኙ የመንሥት ኃላፊዎች ናቸው። እስካሁን ድረስ የሁለት ሰዎች ሕይወት የጠፋ ሲሆን ከ10 በላይ በሚሆኑ ሰዎች ላይ ደግሞ ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት ደርሷል። የወደመውና የተዘረፈው ንብረት ደግሞ ግምቱ ከ30 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር እንደሚልቅም

ወደ ገፅ 3 ዞሯል

**በኢትዮጵያና ሱዳን አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ ውጥረት ነግሷል**

•የኢትዮ-ሱዳን ድንበር በሚቀጥለው ወር እንደሚካለል ሱዳን ትሪቡን ዘገበ

ገፅ 3

**ፖሊስ መምህር ግርማ ወንድሙን በተጨማሪ ግድያ ወንጀል መጠርጠሩን ገለጸ**

ገፅ 3

**በዋግኽምራ የግብርና ባለሙያዎች ስለድርቁ ትክክለኛ መረጃ እንዳይሰጡ ከበላዮቻቸው ተጽዕኖ እንደተደረገባቸው ገለጹ**

ገፅ 3

## ርእሰ አንቀፅ

# ምን ዓይነት የ"ብሔር ብሔረሰብ" በዓል?

የ‹‹ብሔር ብሔረሰቦች›› በዓል መጣ፤ የኢትዮጵያ ታሪክ የሚቀጠቀጥበት፣ የኢሕአዴግ ገድል - ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን ከትርምስና ብተና ያዳነ ድርጅት መሆኑ፣ ኢሕአዴግ በገነባው ሥርዓት አማካይነት ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መፈጠሩ፣ ከኢሕአዴግ መሥመር ውጪ ያለው መንገድ ሁሉ ኢትዮጵያን ወደቀውስና የማያባራ ጦርነት ጎዳና የሚመራ መሆኑ ወዘተ. እጅ እጅ እስኪል የሚነገርበት ጊዜ መጣ!

በመሠረቱ የ‹‹ብሔር ብሔረሰቦች›› በዓል መከበሩን የሚጠላ ኃይል ሊኖር አይችልም። ‹‹ምን ዓይነትና በምን መልኩ የሚከበር በዓል?›› የሚለው ነው ወሳኙ ጥያቄ። ኩነቱን ምክንያት አድርገን ስለኢትዮጵያ ታሪክ፣ ስለሕዝቦች መስተጋብር፣ እግር ከወርች አስረው አላላውስ ስላሉን የአገራችን ችግሮች - ተጣብቶ አለቀን ስላለው ችጋር፣ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ተፈጥሯል እየተባለ በሚደሰኮርበት አገር ውስጥ ዜጎች በአገራቸው እንደሁለተኛ ዜጋ ስለሚቆጠሩበትና መፈናቀል ባህል ስለሆነበት ሁኔታ፣ ስለአገር ሀብት ምዝበራ አረንቋ ወዘተ. በነጻነት የምንመክርበት፣ የምንወያይበትና መፍትሔ መሻት የምንችልበት ቢሆን እሰየው፣ ደግሞ ደጋግሞ ይምጣልን የሚያስብል በሆነ ነበር። ይሁን እንጂ ከእስካሁኑ ተመክሯችን እንደታዘብነው በዓሉ በሕዝብ በዓል ስም የአንድ ቡድን መላዕክነት ወይም ተዓምር ሠሪነት የሚሰበክበት ነው።

በአገራችን ስለብሔራዊ መግባባት ብዙ ተብሏል፤ ስለብሔራዊ ዕርቅ አስፈላጊነት ያለመታከት የሚናገሩ ወገኖችም አሉ። መንግሥት በበኩሉ ማን ከማን ጋር ተጣላና ነው ስለዕርቅ የሚወራው? ይላል። ተመልሶ ደግሞ ስለብሔራዊ መግባባት አስፈላጊነትና በአገራችን መግባባት የተፈጠረ ስለመሆኑ ይናገራል። ‹‹ብሔራዊ መግባባት ተፈጥሯል›› የሚለውን ፌዝ ትተን፤ አስፈላጊ በመሆኑ ጉዳይ ላይ ግን በሁሉም ወገን መስማማት እንዳለ እንገነዘባለን። ትልቁ ጥያቄ፡- ከታሪካችን ጋር ሳንታረቅ፣ ግልጽና የሠለጠነ ውይይት ሳናደርግበት፣ እንዴት ብሔራዊ መግባባት መፍጠር እንችላለን? የሚለው ነው።

የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ስለኢትዮጵያ ታሪክ፣ በአጠቃላይ ስለዘመናዊት ኢትዮጵያ ያላቸው የተዛባ ግንዛቤ ለብሔራዊ መግባባቱ አለመሥመር ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚይዝ ጥርጥር የለውም። ድርጅቱ በተለያዩ ሠነዶቹ እንዳሰፈረውና የድርጅቱ መሪዎች በቃላቸው አበክረው ሲናገሩ እንደሚደመጡት፣ ኢሕአዴግ የብሔረሰቦች መብቶች መከበር ብቸኛው ተቆርቋሪና ፊታውራሪ ነው፤ እርሱና እርሱ የፈጠረው ሥርዓት ከሌለ፣ አገሪቱ በፀረ-ዴሞክራሲያዊና ኪራይ ሰብሳቢ ኃይሎች እጅ ትወድቃለች፤ እንደ አገዛዙ ገለጻ፣ ፀረ-ዴሞክራሲ ኃይሎች ወይ የድሮው ሥርዓት ናፋቂዎችና ትምክህተኞች ናቸው ወይ ደግሞ የለየላቸው ጠባብ ብሔረተኞች ናቸው፤ ሌላ ከኢሕአዴግ የተሻለ ለዚህች አገር የሚያስብ ኃይል የለም ወዘተ.።

አሁንም የአገዛዙ ሰዎች እንደሚሉት፣ ኢሕአዴግ ሥልጣን ከመያዙ በፊት ያሉት ሥርዓቶች በሙሉ ፀረ-ዴሞክራቶችና ለሕዝባቸው የማያስቡ ነበር፤ አንድ ጉደኛ የሥርዓቱ አመራር አባል እንደሉት ደግሞ የኢሕአዴግ ወደ ሥልጣን መምጣት ተራ ሥልጣን የመያዝ ወይም መቀያየር ጉዳይ ሳይሆን፣ ከፈረንሳይ አብዮት፣ ከታላቁ የሩሲያ አብዮትና ከቻይናው አብዮት ጋር የሚተካከል አብዮታዊ ለውጥ ነው። ስለልማታዊ መንግሥትነቱ፣ መንገድ ስለመገንባቱ፣ ግድቦች ስለመሥራቱ፣ ትምህርት ስለማስፋፋቱ፣ ባለሁለት አሐዝ እድገት ስለማስመዝገቡ፣ በአጠቃላይ ወደር የሌለው መንግሥት እየመራ ስለመሆኑ ያለመታከት የሚናገረው አገዛዙ፣ አሁን ያለችውን ዘመናዊት ኢትዮጵያ የገነቧትን መሪዎች መልካም ተግባር ፈጽሞ አያወራም፤ እንዲነገርም አይፈልግም።

ስለ‹‹ታላቁ መሪ›› ሌት ከቀን የሚዘምሩት ሰዎች፣ የዐደዋ ድልን ያህል መላ የጥቁር ሕዝብን ያኮራ ድል ያስገኙት መሪ ስም ማንሳት አይፈልግም። ሠርተውታል ስለሚባለው መጥፎ ሥራ ግን በተጋነነ መልኩ ይጻፋል፤ ይነገራል። የኢትዮጵያን የአገር ምሥረታ ታሪክ ከነችግሩ፣ በአገር ግንባታው ሒደት የተፈጠሩትን ስህተቶች ሳንዘነጋ እናክብረው፤ በታሪኩ ሒደት የተሳተፉትን ዜጎችና መሪዎች በሚገባው መጠን እናክብራቸው የሚሉ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ በድሮው ሥርዓት ናፋቂነት ይወነጅላል። ምኒልክን የምኒልክ ዘመን ሰዎች የፈጠሯትን አገር እያስተዳደሩ፣ ስለነምኒልክ አታንሱብን ማለት ከሐቅ ጋር ፊት ለፊት መላተም ነው።

እውነቱ እንደ ሌሎች አገሮች በኢትዮጵያም የአገር ምሥረታ የተከናወነው በድርድርና በግጭት መሆኑ ግልጽ ነው። በአገር ምሥረታው ሒደት የተጠቀሙ (በድርድር የገቡ) እንዳሉ ሁሉ፣ ተጎጂ የሆኑም ነበሩ። ከዚህ ውጭ ለመሆን የሚችልበት ዕድል ነበረ ወይ? አሜሪካ በታሪኳ አብርሃም ሊንከን በተሳተፉበት የርስ በርስ ጦርነት ያህል ሕዝብ ሞቶባት እንደማያውቅ የታሪክ ባለሙያዎች ይነግሩናል። የዛሬይቱ የዓለም ብቸኛ ልዕለ-ኃያል አገር የተፈጠረቸው፣ ይህን በመሰለ ከፍተኛ ደም በፈሰሰበት ጦርነት መሆኑ ግልጽ ቢሆንም፤ የአሸናፊው ኃይል መሪ አብርሃም ሊንከን እንደነዳግማዊ ምኒልክ ስማቸው አይነሳ አልተባለም። ይልቁንም ዩኒቨርሲቲዎችና ሌሎች ብሔራዊ ድርጅቶች በስማቸው እንዲሰየሙላቸው ነው የተደረገው። የተሠራላቸውና የሚሠራላቸው ቴአትርና ፊልም ደግሞ እስከ አሁንም ቀጥሏል። ለተሸናፊው ወገን መሪ ለሆኑት ጀፈርስም ቢሆን ልዩ ልዩ ብሔራዊ ድርጅቶች ተሰይመውላቸዋል። መሠልጠን ማለት ይሄ ነው! ምርጥ ተመክሮ ማለት ይሄ ነው!

ብሔር/ብሔረሰብ ስለሚባለው ጽንሰ-ሐሳብ ባለን ቁንጽልና በቂ ውይይት ባልተደረገበት ግንዛቤ ምክንያት፣ ያለፉ መሪዎቻችንን (እነሱ እንዲህ ነኝ ሳይሉ!) በብሔረሰብ ከረጢት ውስጥ ከትተን አላስፈላጊ ብቻ ሳይሆን በጣም አደገኛ በሆነ ሁኔታ ፍርድ ለመስጠት እንሞክራለን። ለታሪክ ያለን አተያይም በጣም አደገኛ ነው። ታሪክን ለፖለቲካ መጠቀሚያነት እያዋልን፣ ለቀጣዩ ትውልድ ነቀርሳ እየተከልን መሆኑን መገንዘብ ከሁሉ በላይ በጣም አስፈላጊ ነው።

የብሔረሰቦች በዓል ሁሉም ዜጎች ሊሳተፉበት የሚገባው፣ ምን አተረፍን? ምን አጎደልን? የሚሉትን ጉዳዮች በሰከነ ሁኔታ የምንወያይበት መድረክ እንዲሆንም ያስፈልጋል። ስለአሁኗ ኢትዮጵያ ስንነጋገር ግን ኢትዮጵያን እንደ አገር የፈጠሯትን መሪዎቻችንንም እያሰብን፣ እየዘከርን እና የሚገባቸውን ክብር እየሰጠን መሆን ይኖርበታል። ካለበለዚያ አሁን ኢሕአዴግ እንደሚያደርገው፣ ከታሪክ ጋር ተጣልቶ ብሔራዊ መግባባትን እፈጥራለሁ ማለት በጭራሽ ሊሆን የሚችል አይደለም።

---

## ትዝብት

ሩት አማኑኤል

# አንጀት የሚበሉ ጠቅላይ ሚኒስትር!

ሕዝብ አዋቂ ነው። የፖለቲካ ሶሲዮሎጂስቷ ቴዳ ስኮፖል በሚያሳምን ሁኔታ እንደገለጸችውና በአገራችን በተግባር እንደሚታየው ሕዝብ ዝም ቢልም አፈናን ተቀብሏል ማለት አይደለም። በአፈና ውስጥ ያለ ሕዝብ ዝም ሲል እንድም ብናገርም ለውጥ አላመጣም ማለቱ ነው፤ አንድም ማኩረፉንና መከፋቱን መግለጹ ነው፤ አንድም የተመቻቸ ጊዜ እስኪያገኝ ድረስ አድብቶ መጠበቁ ነው። ሕወሓት/ኢሕአዴግ ከምርጫ 97 በፊት የነበረውን ሁኔታና የኢትዮጵያን ሕዝብ ማኅበራዊ ሥነልቦና ባለማወቅ በሙሉ ልቡ እንደሚያሸንፍ አምኖ የምርጫውን ሂደት ለቀቅ አደረገው። አድብቶ ሲጠብቅ የነበረው ሕዝብ ዕድሉን ሲያገኝ አደባየው። በሚያሳፍር ሁኔታ የኢትዮጵያ ናሙና በሆነችው አዲስ አበባ በነጻ ምርጫ መቶ በመቶ ተዘረረ፤ እርቃኑን ቀረ! በእርግጥ ከምርጫ 97 በኋላ በተካሄዱት ምርጫ ተብየዎች ኢሕአዴግ ዓይኑን በጨው አጥቦ መቶ በመቶ አሸንፌያለሁ ሲለን ከርሟል። ሐቁን ግን እኛም ኢሕአዴጋውያንም በሚገባ እናውቀዋለን።

ከምርጫ 97 በኋላም ሕዝቡ ዝም ብሏል፤ አሁንም እንደለመደበት ጊዜ ይጠብቃል እንጂ አፈናን ተቀብሏል ማለት ግን አይደለም። ሥርዓቱን የሚደግፉ የሉም አይባልም። በደንብ አሉ። የብሔረሰብ ፖለቲካ ያናወዛቸውና በብሔረስብ ትስስር የከበሩት ጠንካራ የሥርዓቱ ደጋፊዎች ናቸው። ግን በጣም ጥቂት ናቸው። ብዙሃኑ ሕዝብ አሁንም ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ጋር አይደለም። ጥርጥር የሌለው ነገር ነው።

ለዚህች ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ከባህር ዳር ከተማ ነዋሪዎች ጋር በመልካም አስተዳደር ችግሮች ላይ በተወያዩበት ወቅት ያነሱት ነገር ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ‹‹ቢያንስ ጉቦ አትስጡ፤ ሰጪ ከሌለ ተቀባይም የለም›› በማለት ስለሙስና ሲናገሩ ተሰምቷል። የባህር ዳር ከተማ ነዋሪዎች በአቶ ኃይለማርያም ንግግር ‹‹ታላቅነትና መሠረታዊነት›› ላይ የተስማሙ ቢመስሉም ችግሩ የሥርዓት ችግር እንደሆነ በሚገባ ያውቁታል። ግን በአንድ በኩል ስለሥርዓት ችግር ቢናገሩ ምን እንደሚመጣባቸው ስለሚያውቁ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የችግሩን ምንጭ ቢናገሩም የሚሰማቸው እንደሌለ ስለሚረዱ ዝምታን መርጠው ይልቁንም በአቶ ኃይለማርያም ንግግር የተደመሙ መስለው ከስብሰባው ወጥተዋል። የሙስና ችግር፣ የመሬት ዘረፋና ቅሚያ ችግር፣ የመልካም አስተዳደር ገደል መግባት ወዘተ. የሥርዓት ችግር እንደሆነ፣ አገዛዙ ከዚህ አረንቋ ውስጥ የተዘፈቀው በራሱ ባለሥልጣናት አጋፋሪነትና መሪነት እንደሆነ አቶ ኃይለማርያምም አሳምረው ይገነዘባሉ። የሚያሳዝነው ለስሙ ጠቅላይ ሚኒስትር ተባሉ እንጂ ማፊያውን ቡድን ሊቆጣጠሩትና ልጓም ሊያበጁለት የሚችሉበት አቅም ጨርሶ የላቸውም። ይህንም በሚገባ ይገነዘቡታል። ስለዚህም ዋናውን ጉዳይ ትተው በጭፍጫፊው ላይ ያተኩራሉ። ሕዝብ ሳይቸግረው ጉቦ ይሰጥ ይመስል ‹‹ጉቦ ሰጪ ከሌለ ተቀባይ አይኖርም›› የሚሉት ተረት ተረት ይናገራሉ።

ለዚህ ነው ከወዳጆቼ ጋር ስንወያይ፣ ‹‹እኚህ ሰውዬ ሊታዘንላቸው እንጂ ሊታዘንባቸው አይገባም›› እያልኩ አስተያየት የምሰጠው። በኔ ግምት ሰውዬው አቅም አልባ ከመሆናቸው የተነሳ ሥልጣን አልፈልግም ብለው መውረድ ሁሉ የሚችሉ አይመስለኝም። አንጀት የሚበሉ ጠቅላይ ሚኒስትር!

---


**በዲኦንሔር ፐብሊሺንግ ሚዲያ እና ኮምኒኬሽን ኃላ.የተ.የግ. ማኅበር እየተዘጋጀ የሚቀርብ ሳምንታዊ ጋዜጣ**

**ሥራ አስኪያጅ**
አበበ ውቤ

**ዋና አዘጋጅ**
ሙሉቀን ተስፋው
0910159783
mulukentesfaw@gmail.com
የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 09/297


**ሪፖርተር**
ትሑት ጥላሁን

**አምደኞች**
መስከረም አበራ
ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)
ሩት አማኑኤል
መብራቱ በላቸው
በሪሁን አዳነ
ታዲዮስ ታንቱ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 08
ቤ/ቁጥር 471
ስልክ፡ 0910159783
0919396240

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ስልክ፤ 0911 18 09 33

**አታሚ**
<<ሶፍ ሚክ ማታሚያ ቤት
ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 04
የቤት ቁጥር 64

# በኢትዮጵያና ሱዳን አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ ውጥረት ነግሷል

## •የኢትዮ-ሱዳን ድንበር በሚቀጥለው ወር እንደሚካለል ሱዳን ትሪቡን ዘገበ

በሚቀጥለው ወር ይካሄዳል ተብሎ የሚጠበቀውን የኢትዮ ሱዳን ድንበር ማካለል ወሬ በሱዳን ትሪቡን መገለጹን ተከትሎ በመተማና በአርማጭሆ አካባቢ ውጥረት መንገሡ ነው እየተገለጸ ያለው፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ከኢትዮጵያ ምንም ዓይነት መሬት ተላልፎ አልተሰጠም እያለ ቢቆይም በተቃዋሚ ወገኖችና ለጉዳዩ ቅርበት ባላቸው አካላት ዘንድ ተዓማኒነት ግን አልነበረውም፡፡ ሱዳን ትሪቡን የኢትዮጵያውን ጠቅላይ ሚኒስትር ዋቢ አድርጎ እንደገለጸው የድንበር ማካለሉ ሥራ በሚቀጥለው ወር ይጠናቀቃል ብሏል፡፡ የሱዳንና የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የድንበር ማከለሉን ሥራ ለማከናወን ቀን እንዲቆርጡ በሁለቱም ርእሳነ ብሔሮች ታዘዋል ሲል አስነብቧል፡፡ ሱዳን ትሪቡን በድምበር አካባቢ ያለውን መሬት የሁለቱም አገሮች ገበሬዎች በይገባኛል ስሜት ግጭት እየፈጠሩ መሆኑን በማውሳት የ250 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋትና የ600,000 አክሪስ ለም መሬትን ያካተተ ነው ብሏል፡፡ ዘገባው ድንበሩ የተሠራው በ1908 በኢጣሊያና በእንግሊዝ ቅኝ ገዥ ኃይሎች እንደሆነ የጠቀሰ ሲሆን የድንበር ማካለል ሥራ የቅኝ ግዛት ውሎችን መሠረት ባደረገ መልኩ እንደሚካለል ግን ያለው የለም፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ባለፈው ሳምንት የኦነግ ታጣቂዎችን ለመያዝ በሚል በኬንያ ክልል በመግባት ሦስት የኬንያ ፖሊሶችን የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ገድሏል መባሉን ተከትሎ በቀጠናው ውጥረት እንዳለ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን እየገለጹ ነው፡፡ በኬንያ የሚታተሙ ጋዜጦች የሁለቱን አገራት ግንኙነት ሳያሻክረው እንደማይቀር ሲገልጹ ሰንበተዋል፡፡

በምዕራብ ሐረርጌና በሶማሊ ክልል ድምበር አካባቢ በከብቶች የግጦሽ መሬት ምክንያት በተነሳ የጎሳ ግጭትም የሰዎች ሕይወት ማለፉ ነው የተነገረው፡፡ ከቦታው ለዝግጅት ክፍላችን የገለጹት ታማኝ ምንጮች ከባለፉት አራት ወራት ወዲህ አካባቢው የተረጋጋ አለመሆኑን ተናግረዋል፡፡ የፌደራል መከላከያ ኃይል ከገባ በኋላ የተወሰነ መረጋጋት ቢፈጠርም አካባቢው እስካሁን በውጥረት የተሞላ ነው ተብሏል፡፡

# ፖሊስ መምህር ግርማ ወንድሙን በተጨማሪ ግድያ ወንጀል መጠርጠሩን ገለጸ

መምህር ግርማ ወንድሙ በተጠረጠሩበት የማታለል ወንጀል የተፈቀደው ዋስትና ላይ የመርማሪ ፖሊስ ቡድኑን ይግባኝ ችሎት ውድቅ አድርጎት ነበር፡፡ አዲስ አበባ ፖሊስ የምርመራ ቡድን ከተጠርጣሪው ቤት የተገኙ 14 ሲም ካርዶችን ለኢትዮ ቴሌኮም ልኬ መልስ እየጠበቅኩ ነው በማለት የ14 ቀን የጊዜ ቀጠሮ ቢጠይቅም ፍርድ ቤቱ ዋስትና የሚያስከለክል አይደለም በማለት ዋስትና መፍቀዱ ይታወቃል፡፡

መርማሪ ቡድኑ ይግባኝ ጠይቆ ዋስትናውን በማሳገድ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ቢያቀርባቸውም ፍርድ ቤቱ የመምህር ግርማን የዋስትና መብት አጽንቶ በማታለል ወንጀል 50 ሽህና በሀሰተኛ ሰነድ በማገልገል ደግሞ የ40 ሽህ ብር በድምሩ የዘጠና ሽህ ብር ዋስ አስይዘው መውጣት እንዲችሉ ፈቅዷል፡፡

ሆኖም የአዲስ አበባ ፖሊስ ምርመራ ቡድን መምህር ግርማን ከተከሰሱበት ወንጀል በተጨማሪ በግድያ ወንጀል ጠርጥሬያቸዋለሁ በማለት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ያመለከተ ሲሆን ጉዳያቸውን ለማየት ትንናት ሕዳር 20 ቀን ፍርድ ቤት ቀርበዋል፡፡ መምህር ግርማ ወንድሙ ይህ ዜና እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ በእስር ላይ ይገኛሉ፡፡

# በዋግኽምራ የግብርና ባለሙያዎች ስለድርቁ ትክክለኛ መረጃ እንዳይሰጡ ከበላዮቻቸው ተጽዕኖ እንደተደረገባቸው ገለጹ

ድርቁ በአካባቢው በሰውና በእንስሳት ላይ ያስከተለውን ችግር ለመግለጽ አንችልም የሚሉት የግብርና ባለሙያዎች ያለውን ሁኔታም በፌስቡክ ፎቶ አንስተን እንዳንለቅና ለሚዲያም እንዳንናገር ተጽዕኖ እየደረሰብን ነው ሲሉ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል፡፡ ባለሙያዎቹ እንደሚሉት ለተጎጂዎችም በቂ የምግብ እህል አልቀረበም ብለዋል፡፡

ለምን መረጃውን ይፋ ማድረግ እንደማይፈለግ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ ‹‹ገጽታን ያበላሻል ከሚል ስጋት ሲሆን እኛ ግን በምናየው ነገር በጣም ተሳቀናል›› ብለዋል፡፡ ከተቀመጡበትና ከተኙበት መነሳት የሚሳናቸውን ሰዎችና እንስሳት መመልከት ሕመም እንደሆነባቸው የሚናገሩት ባለሙያዎቹ በየቀኑ የሚረግፉ እንስሳት ቁጥር ከፍተኛ ነው ብለዋል፡፡ ሕዝብ በተራበበት በሰቆጣ ከተማ የብአዴንን 35ኛ ዓመት ለማክበር የተደረገው ዝግጅት ሕዝቡ ሁሉ አዱኛ የሞላለት እንጂ የተራበ ሰው ያለበት አይመስልም ነበር በማለት ትዝብታቸውን ገልጸዋል፡፡

# ፍርድ ቤት የጋዜጠኛ ጌታቸው ወርቁን መቃወሚያ ሳይቀበለው ቀረ

የኢትዮ-ምህዳር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጌታቸው ወርቁ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ 6ኛ ወንጀል ችሎት በተከሰሰበት ወንጀል ያቀረበው የመጀመሪያ መቃወሚያ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጽሕፈት ቤት በኢትዮ-ምህዳር ጋዜጣ በግንቢት ወር 2007 ዓ.ም. በወጣ ዘገባ የደብሩን ስም አጥፍቷል በሚል ክስ የመሠረተበት ሲሆን ጉዳዩን ሕዳር 21 ቀን 2008 ዓ.ም. ያየው ችሎት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡

የአቶ ጌታቸው ወርቁ የሕግ ጠበቃ አቶ በኃይሉ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት ጋዜጣው በዘገባ መልክ የሠራው በሌላ ምንጮች በተደጋጋሚ የተቀሰ መሆኑና ዘገባው ቀጥታ የሚገልጸው ግለሰቦችን እንጂ ቤተ ክርስቲያኗን የማይነካ ስለሆነ እንዲሁም በቃለ አዋዲው መሠረት መክሰስ ያለበት ሰበካ ጉባኤው እንጅ አስተዳደር ጽሕፈት ቤቱ መሆን የለበትም የሚሉ ሦስት መቃወሚያ ያቀረቡ ቢሆንም ውድቅ እንደተደረገባቸው ገልጸዋል፡፡ ከሁለት ሳምንታት በፊት ለንባብ በበቀው የኢትዮ ምህዳር ጋዜጣ ላይ አሁንም ድጋሚ ተያያዥ ዘገባ መሥራቱን የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ጠበቃ አቅርቧል፡፡ አቶ ጌታቸው ወርቁ ሙያዊ ሥራዬን አከናወንኩ እንጅ ምንም የሰራውት ወንጀል የለም ሲል ተከራክሯል፡፡ ችሎቱ ሁለቱም ሕግና ሥርዓት ተከትለው ሥራቸውን እንዲያከናውኑ በማሳሰብ ለሕዳር 25 ቀን 2008 ዓ.ም. ከቀኑ በ8፡00 ምስክሮች እንዲሰሙ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

# አቶ አብርሐም ጌጡ ወደ ቂሊንጦ ማረሚያ ቤት ተዛወሩ

በአቶ ማሙሸት አማረ ካቢኔ የመኢአድ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ የነበሩት አቶ አብርሐም ጌጡ ሕዳር 14 ቀን 2008 ዓ.ም. በአራዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ሰባራ ባቡር) ቀርቦ ይግባኝ ተጠይቆበታል፡፡ የአራዳ ምድብ ችሎት ለሕዳር 11 ቀን ቀጥሯቸው የነበረ ቢሆንም ሕዳር 7 ቀን 2008 ዓ.ም. ፍርድ ቤቱ በ5000 ብር ዋስ በነጻ እንዲለቀቁ መወሰኑ ይታወቃል፡፡ አቶ አብርሐም ጌጡ በሽብር ወንጀል ለ6ኛ ጊዜ ፍርድ ቤት የቀረቡ ሲሆን ከተያዙበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ መዝገቦችና ፍርድ ቤቶች ለ11ኛ ጊዜ መቅረባቸውን ጠበቃቸው ገልጸዋል፡፡

አቶ አብርሐም በሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ቤታቸው ተበርብሮ ከታሰሩ በኋላ እስከ ሐምሌ ድረስ በ5ኛ ፖሊስ ጣቢያ በእስር ላይ ቆይቶ ነበር፡፡ ከሐምሌ 12 ቀን ጀምሮ ለሦስት ወራት ያክል በማዕከላዊ ከቆዩ በኋላ ሕዳር 17 ቀን 2008 ዓ.ም. ወደ ቂሊንጦ ማረሚያ ቤት ተዛውረዋል፡፡ አቶ አብርሐም በሽብር ተጠርጥረው የታሰሩ ሲሆን ክሳቸው ‹‹የሐሰት ወሬ በመንዛት አመጽ ማነሳሳት›› ወደሚል ክስ ተለውጧል፡፡ ትናንትና ሕዳር 20 ቀን 2008 ዓ.ም. ፍርድ ቤት በድጋሚ የቀረቡ ሲሆን ወደ ማተሚያ ቤት ቀድመን በመግባታችን ምክንያት የፍርድ ቤት ውሎውን ማካተት አልቻልንም፡፡

# የዜጎች መፈናቀል. . .

ተመልክቷል፡፡

ሰመጉ ባዘጋጀው ጋዜጣዊ መግለጫ ከተገኙ ተጎጂዎች መካከል አቶ ዓለሙ የተባሉ የአገር መከላከያ ሠራዊት አባል የነበሩ ግለሰብ በሰጡት ምስክርነት ‹‹የወረዳው ፖሊስ አዛዥ ከፊቴ በጥይት መትቶ ሲገድለው እንዲተው ብጠይቀውም ‹አማራ እኮ ነው ምን አገባህ› የሚል መልስ ሰጠኝ፡፡ እኔ ሰላም ለማስከበር ላይቤሪያ ድረስ ዘምቻለሁ፤ ሆኖም በአገሬ ላይ ሰላም ማጣቴ ያሳዝናል›› በማለት በይፋ ሲናገር ታዳሚዎችን ሁሉ በሐዘን አንገት አስደፍቷል፡፡ አቶ ዓለሙ ከአማራና ኦሮሞ ቤተሰቦች የተገኘ ቢሆንም ድርጊቱን ተቃውመሃል በሚል ለ22 ቀናት ታስሮ እንደተሰቃየም አክሎ ገልጿል፡፡ የሟች አቶ ዳመና ግዘው ወንድም በበኩላቸው ‹‹ወንድሜ ልጄን እሑድ ሊድር ቅዳሜ በፖሊስ አዛዡ ተገደለብኝ›› በማለት በእንባ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል፡፡ ሀብት ንብረታቸው የተቃጠለው ከእያንዳንዳቸው 300 ብር ተሰብስቦ በተገዛ ነዳጅ እንደሆነ የሚገልጹት ተጎጂዎች በእስራት ወቅት ብልታቸውና ጡታቸው በፒንሳ መጠምዘዝ ስቅይት እንደተጋለጡ ተናግረዋል፡፡ እስካሁንም ድረስ ወደ ቀያቸው አለመመለሳቸውን ነው የተናገሩት፡፡

ሰመጉ በጋዜጣዊ መግለጫው የተዳሰሰው ደግሞ በአፋር ክልል በአሳይታ ወረዳ በተንዳሆ ስኳር ፕሮጀክት መሥፋፋት ምክንያት በርካታ ዜጎች የቴምር ዛፋቸው ተጨፍጭፎባቸዋል ተብሏል፡፡ የስኳር ፕሮጀክቱ ማስፋፊያ የ111 ከፊል አርብቶ አደሮች ንብረት የሆነ ከ8500 በላይ የቴምር ዛፍ የወደመ ሲሆን በገንዘብ ሲተመንም ከ596 ሚሊዮን ብር በላይ እንደሆነ ነው የተገለጸው፡፡ ሰመጉ በ138ኛ መግለጫው አፋሮቹን መሠረት አድረጎ እንደገለጸው የአንድ ቴምር ዛፍ ሲቆረጥ የሚከፈለው የካሳ መጠን 7 የጋማ ከብት ነው ብሏል፡፡ ከአፋር ክልል የመጡት ተጎጅዎች በሰጡት ምስክርነት ‹‹ቴምር ለእኛ ምን ማለት እንደሆነ ለመረዳት እኛን መሆን ያስፈልጋል፡፡ ከምንመገበው ጀምሮ ቤታችንና መኝታችን የምንሰረው በቴምር ነው›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡ እስካሁን ድረስ ምንም አይነት ካሳ ያልተሰጣቸው ተጎጅዎች አካባቢውን ለቀን ወደ ጅቡቲ አሊያም ሶማሊላንድ እንድንሰደድ ይፈለጋል ሲሉ ተናረዋል፡፡ ሰመጉ ከመንግሥት በኩል ምንም ዓይነት የእርምት እርምጃ ባለመወሰዱ ይህን ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት ተገድጃለው ብሏል፡፡

# በማኅበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን አገልግሎት አሰጣጥ ጡረተኛው እየተማረረ ነው

በብሩክ ከበደ

የማኅበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጀመረውና እሰጠዋለሁ በሚለው አገልግሎት ጡረተኛው እየተማረረ ነው፡፡ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ጡረተኛው በሚኖርበት አካባቢ አገልግሎቱን እንዲያገኝ በሚል የከፈታቸው ማዕከላት የጡረተኛውን አቅምና ቦታዎቹን ለይቶ ለማግኘት እንዳደረገባቸው ጡረተኞች እየገለጹ ነው፡፡

በተለይ በልደታ ክፍለ ከተማ የሚገኙ ዋና ባለመብቶች፣ ወራሾችና ተወካዮች የማኅበራዊ ዋስትናው ቅርንጫፍ አዲስ የከፈተው ቢሮ ሳር ቤት ከቫቲካን ኢምባሲ ፊትለፊት ወደ ውስጥ 700 ሜትር በላይ ገብቶና እንደገና ወደ ግራ ከ400 ሜትር በላይ በሚወስደው ተዳፋት ሥር በሚገኝ ግቢው ጠባብና አዲስ የተገነባ የግለሰብ ቪላ ተከራይቶ ሊሰጥ የተዘጋጀው አገልግሎት ከወዲሁ ጡረተኛውን እያማረረ ነው፡፡

ቦታው ታክሲም ሆነ ባጃጅ የማይገባበትና ቢሮውን ለይቶ ለማግኘት አስቸጋሪ የሆነውን ቦታ ዘጋቢው በስፍራው ተገኝቶ የተመለከተና ለጡረተኞች እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን የተመለከተ ሲሆን በቦታውም በተለያየ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ጡረተኞች ጡረተኛውን ታሳቢ ያደረገ ሳይሆን ግለሰቦች ለመጠቃቀም የዘረጉት ሰንሰለት እንደሚሆንና ይህም አንዱ የመልካም አስተዳደር እጦት መሆኑን ገልጸው አመራር ላይ ያሉትም ጡረተኛ ማለት ምን ማለት እንደሆነም የሚያውቁ አይመስለኝም ሲሉ ቅሬታቸውን ይገልጻሉ፡፡

አንድ ስማቸው እንዲገለጽ የማፈልጉና የጡረታ መቀበያ ካርድ ሊለውጡ የመጡ አንጋፋ የሕክምና ባለሙያ የመንገዱ ርቀት ሪህ፣ ልብ ድካም፣ ስኳር፣ ኩላሊትን ጨምሮ ማየትና መራመድ የተሳናቸውንና ሌላም ተዛማጅ ሕመም ታማሚ በሆኑ ጡረተኞች ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል መሆኑን መሥሪያ ቤቱ አለመረዳቱ በጣም የሚገርም ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

በጊዜው ዘጋቢው የጡረተኞችን ማኅበር በየወሩ የሚያሳትመው ጋዜጣ አዘጋጅ የሆነውን አቶ አባተ ማንደፍሮን ጨምሮ ለተለያዩ የማኅበሩ አባላት የጡረተኛውን ብሶት ያቀረበ ሲሆን እነርሱም ለሚመለከተው አካል ቅሬታውን እንደሚያስተላልፉ ቃል ገብተዋል፡፡

ማኅበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በዚህ ዓመት ካርድ ለሚለውጡ የሲቪል፣ የሚሊታሪ እንዲሁም የሕግ ባለመብቶች (ወራሾች) ካርድን ሲቀበሉ በጣት ፊርማ እንዲያስቀምጡ መደረጉ በተለይ በተማሩት ጡረተኞች ዘንድ ቅሬታን የፈጠረ ሲሆን ለዚህም ይህ ነው የተባለ ምክንያትና ማብራሪያ ለጡረተኛው አለመስጠቱ ሌላው ቅሬታ የፈጠረ ጉዳይ ነው፡፡

# የኢፈና ሥርዓትን መሸከም

የማኅበራዊ ሳይንስ ምሁራንን በሰፊው ሲያከራክር የኖረና በማከራከር ላይ ያለ፣ ብዙዎችም በቂ መልስ ያላገኙለት ጉዳይ አለ። አምባገነኖች በብዙኀኑ ሕዝብ የተተፉ ናቸው፤ ይሁን እንጂ ደግሞ ብዙኀኑ ሕዝብ እየጠላቸውም ቢሆን ለረዥም ዓመታት በሥልጣን ላይ ይቆያሉ። ለምን? እንዴት? በኩባ፣ በሊቢያ፣ በጋቦን፣ በግብጽ፣ በዚምባብዌ፣ በአንጎላ፣ በሱዳን፣ በዩጋንዳ፣ በኤርትራ፣ በኢትዮጵያ ወዘተ. የኢፈና አገዛዞች ከሁለት ዐሥርት ዓመታት በላይ በሥልጣን ላይ መቆየት ችለዋል። የዜጎችን መሠረታዊ መብቶች አፍነው ሕዝብ እያስለቀሱና እያደሙ እንዲኖሩ ዋና ዋና የመኮርኮሚያ ጡንቻዎችን (የደህንነትና የጸጥታ ኃይሉን፣ ሠራዊቱን ወዘተ.) በእጃቸው ማድረጋቸው ከፍተኛ አስረዋጽኦ ማድረጉ የሚካድ ባይሆንም፣ ዕድሜያቸው ዘልዛላ የሆነው በዚህ ምክንያት ብቻ ነው ማለት ግን ጨርሶ አይቻልም። ምሁራን የሚጠቅሷቸው ብዙ ነጥቦች ቢኖሩም ሦስቱ ምክንያቶች (ምሰሶዎች) ጎላ ብለው የወጡና ብዙዎች የሚስማሙባቸው ናቸው። እነዚህን ነጥቦች ይዘን በአገራችን የተተከለውን አገዛዝ እንፈትሸው፡-

## መኸገር ከበርቴ

ከአፈና አገዛዞች የሥልጣን መሠረቶች መካከል አንዱ በጥቅም ትስስሮሽ በአንድ ጀንበር የሚከብረው እና ከአገዛዙ ጋር በመጠጋጋት የአገርን ሀብት እንደመኸገር የሚመጠው ደራሽ ከበርቴ ነው። ይህ ኃይል በአገዛዙ ደጋፊነቱ ወይም ከባለሥልጣናት ጋር ተጠጋግቶ የከበረ በመሆኑ የሀብቱ ምንጭም ጠባቂም የሆነውን የአፈና ሥርዓት ታጥቆ መደገፉ ያለና የሚጠበቅ ነው። በአምባገነናዊ ሥርዓቱ አማካይነት ከዘረፈው የአገር ሀብት ውስጥ የተወሰነውን ለገኸው ፓርቲና ለፓርቲው አመራሮች ያካፍላል። ይሁን እንጂ ሀብት ያፈራበትን መንገድ ስለሚያውቀው ሁልጊዜም እንባነነና እንደተቅበዘበዘ ነው፤ ስለሆነም አገዛዙን ክፉ እንዳያገኘበት ሌት ተቀን ይሠራል። ይኸው ኃይል ምርጫ በሚካሄድበት ወቅት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ከተቻለ በጥቅም ደልሎ ከተቃውሞው ጎራ እንዲርቁ ያደርጋል፤ ካልሆነ ደግሞ ያስፈራራል፤ እስከመግደልም ይደርሳል።

መኸገሩ የከበርቴ ቡድን የተነሳበትን ደረጃ ዘንግቶ በከፍተኛ ምቾትና ድሎት ወስጥ ስለሚኖር ሕዝቡ ሁሉ እንደእርሱ በቅንጦት ውስጥ የሚኖር ይመስለዋል፤ በዚህ ምክንያት ሁልጊዜም ስለአገዛዙ የሚያወራውና የሚያስወራው መልካም መልካሙን ነው። የሕዝቡ ምሬት ከልክ አልፎ በሥርዓቱ ላይ በሚነሳበት ወቅት የመኸገር ከበርቴው ሰልፍ ከአገዛዙና አገዛዙን ከሚጠብቀው ኃይል ጋር ይሆናል። የሕዝቡ ትግል ይበልጥ እየጋለ፣ እየጎመራና ወደማይመለስበት ደረጃ እየደረሰ መሆኑን ሲያውቅ ደግሞ የሚያሸሸውን ያህል ንብረት ካሸሸ በኋላ ቀኝ ኋላ ዙር ይልና ሰልፉን ከብዙሃኑ ሕዝብ ጋር ያደርጋል። የዚህ ዓይነት ክስተት በብዙ አገሮች የታየ ነው። የቅርብ ጊዜውን ብንጠቅስ በቱኒዚያ፣ በግብጽና በሊቢያ የሆነው ይኸው ነው።

ከላይ የተጠቀሰውን መነሻ ይዘን የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ፣ በአገራችን ከኢሕአዴግ ጋር ተጠጋግቶ የከበረውን ደራሽ መኸገር የከበርቴ ቡድንና ይኸው ቡድን በአገራችን ተጠያቂነትን የሚያሰፍን የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዳይመሠረት የሚጫወተውን አፍራሽ ሚና መገምገም እንችላለን። በምርጫ 97 ወቅት ብዙ ‹‹ልማታዊ ባለሀብቶች›› ወደተለያዩ የአገራችን ገጠር አካባቢዎች እየተዘዋወሩ አንሶላና ብርድ ልብስ እያደሉና ከብት አርደው ቁርጥ እየጋበዙ አርሶ አደሩ ኢሕአዴግን እንዲመርጥ ሲለምኑ፣ ሲያግባቡና ሲያስፈራሩ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም። የኢትዮጵያ አርሶ አደር ሕይወት ያስተማረው አርሶ አደር በመሆኑ የሚደረገው ሁሉ ለምን እንደሚደረግ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ብርድ ልብሱና አንሶላውን



ተቀብሎ፣ ቁርጡንና ክትፎውንም ተጋብዞ ሲያበቃ የሚሠራውን ሠራ እንጂ ብዙ ነገር ተደርጎ ነበር።

ከየብሔረሰብ ድርጅቶች ጋር በመሞዳሞድ መሬት የሚቀራመተውና የአገር ሀብት የሚመዘረው አገዛዝ ዘራሽ ከበርቴ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመሥረት የሚደረገውን ትግል በማኮላሸት በኩል ያለውን አቅም መዘንጋትና አገዛዙንና ራሱን ለመጠበቅ እስከምን ድረስ ሊሄድ እንደሚችል አለማገናዘብ ትልቅ ድክመት ይሆናል።

## ክፍፍል

ሁለተኛው የአፈና አገዛዞች የሥልጣን መሠረት የሕዝብ መከፋፈል ነው። ከላይ የተጠቀሱት አብዛኞቹ የአፈና አገዛዞች የሚገዙትን ሕዝብ በጎሳ፣ በብሔረሰብ፣ በሃይማኖት ወዘተ. የሚከፋፍሉና በተለያዩ ጊዜያት አንዱን እየደገፉ በሌላው ላይ የሚዘምቱ፣ የሕዝብ ጥላቻ፣ አለመተማመንና ግጭት ሰርግና ምላሻቸው ሆኑ በአብዛኛው አንድ ብሔረሰብን ወይም የሃይማኖት ተከታይ ማኅበረሰብን ‹‹የሚወክሉ›› ናቸው። ሕዝቡ አንድ የሆነ እንደሆነ ሥልጣናቸው ባዶ እንደሚቀርና በጸጥታና መከላከያ ኃይሉ ላይ ብቻ እንደሚንጠላጠሉ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ በሕዝቡ መካከል መተማመን እንዳይኖር፣ ጥርጣሬና ጥላቻ እንዲነግስ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። በተለያዩ ጎሳዎችና የሃይማኖት ተከታዮች መካከል ግጭት ሲነሳ ገላጋይና ሽምጋይ ሆነው ከተፍ ይላሉ። ‹‹እኛ ባንኖር አልቃችሁ ነበር፤ ወደፊትም እኛ ከሌለን ህልውናችሁ አደጋ ላይ ነው›› ይላሉ።

አገራችን ኢሕአዴግ በሚከተለው የጠራ ፖሊሲና ስትራቴጂ ምክንያት ከእልቂትና ብተና ተርፋ በሕዝቦች መካከል ታይቶ የማይታወቅ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ስለመፈጠሩ እጅ እጅ እስኪለን ድረስ የተነገረን ቢሆንም ተጨባጭ እውነታው ለማናችንም በጣም ግልጽ ነው። የማንነት ፖለቲካ መረን በለቀቀ ሁኔታ ሲራገብና ሲኮተኮት በመክረሙ በዜጎች መካከል የሰፈነው ዴሞክራሲያዊ አንድነት ሳይሆን ጥርጣሬና አለመተማመን ነው። ዴሞክራሲያዊ አንድነት ተፈጥሯል፣ ‹‹እዚህም እዚያም ኪራይ ሰብሳቢዎች የሚፈጥሩት ችግር ቢኖርም በሕዝቦች መካከል መተማመንና ፍቅር ጨምሯል››፣ ወዘተ. እየተባለ የሚነገረው መሠረተ ቢስ ዲስኩር ባዶ ጫጫታ መሆኑ የሚገለጥልን ኢትዮጵያውያን በአገራቸው እንደሁለተኛ ዜጋ እየተቆጠሩ ከቤት ንብረታቸውና ከኖሩበት አካባቢ በጠራራ ጸሐይ በመፈናቀል ላይ መሆናቸውን ስንመለከት እንዲሁም ዜጎች ለደረሰባቸው ግፍ ‹‹አቤት›› የሚሉበት ሲያጡ ይልቁንም ‹‹አቤት›› የሚባልበት የመንግሥት አካል ራሱ የጥቃቱ መሪ ተዋናይ መሆኑን ስንታዘብ ነው።

በሕዝቦች መካከል የተተከለውን፣ ሥር በመስደድ ላይ ያለውንና ፍሬም ማፍራት የጀመረውን የልዩነት ፖለቲካ ደረጃ አቃልሎ ማየትም አገራችን የገባችበትን አረንቋ በሚገባ አለመገንዘብ ነውና ዋጋ ያስከፍላል።

## የተቃውሞው ጎራ ሁኔታ

ቀዝቃዛው ጦርነት በአሜሪካና አጋሮቹ የበላይነት ከተጠናቀቀ በኋላ ሊብራል ዴሞክራሲ በዓለም ላይ ‹‹ያለተወዳዳሪ›› ነግሷል። ሊብራል ዴሞክራሲን የሚቃወሙት ኮምኒስቶችና የለየላቸው አምባገነኖች ሳይቀሩ የሊብራል ዴሞክራሲ መገለጫ የሆነውን መድበለ ፓርቲ ሥርዓት ሳይወዱ በግዳቸው መቀበላቸውን ሲገልጹና በሕገ መንግሥት ደረጃ ሲያሰፍሩ ተስተውለዋል። የሕወሓት/ኢሕአዴግ ከአልባኒያ ኮምኒዝም አቀንቃኝነት ወደ ነጭ ካፒታሊዝም ተከታይነት ቀኝ ኋላ ዙር እንደ አብነት ሊጠቀስ ይችላል። ይሁንና ደግሞ እነዚህ ኃይሎች የመድበለ ፓርቲና መድበለ ሐሳብ ሥርዓትን እንደሚቀበሉ ቢያውጁም፣ ተፈጥሯቸውና የቆሙበት ማኅበራዊ መሠረት ዴሞክራት እንዲሆኑ አይፈቅድላቸውምና ወቅቱን እየጠበቁ የይስሙላ ምርጫ እያደረጉ በከፍተኛ የድምጽ ልዩነት አሸነፍን ማለትን ባህል አድርገውታል። ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ የሚደረግበትን ሁኔታ እንደሚቀበሉና ለዚህም እንደሚሠሩ ገልጸው ሲያበቁ ሕዝብ ሲደራጅና ተቃዋሚውን ኃይል ሲደግፍ አይቀጡ ቅጣት ወደ መቅጣቱ ይሄዳሉ።

በሌላ በኩል በሕዝቡ መካከል እንደተከሉት ሁሉ በተቃዋሚ ድርጅቶችም ውስጥ የማንነት ፖለቲካ ሥር እንዲሰድና ተቃዋሚው ኃይል እንዳይተባበር ከፍተኛ ጥረትም ያደርጋሉ። በዚህ ረገድ በአገራችን ሲዘራና ሲኮተኮት የከረመው የልዩነት ፖለቲካ ወደተቃውሞው ጎራም ተዛምቶ ተቃዋሚው ኃይል እንዳይተባበርና አብሮ እንዳይሠራ ከፍተኛ መሰናክል መፍጠሩ ግልጽ ነው። ባለፉት ሁለት ዐሥርት ዓመታት በአገራችን የተፈጠሩት ትብብሮች፣ ቅንጅቶችና ኅብረቶች መክነው የቀሩት በዚህ ምክንያት መሆኑም ብዙም የሚያከራክር አይደለም።

የሕዝቡና የተቃውሞው ጎራ የልዩነት ፖለቲካ ሰለባ መሆኑ አገዛዙን እጅግ እጅግ ጠቅሞታል። ኢትዮጵያ ውስጥ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን የደገፉና የመረጡ ዜጎች የሚደርስባቸው አበሳ በጣም ከባድ መሆኑና የተቃውሞው ጎራም የልዩነት ፖለቲካ ሰለባ በመሆኑ ምክንያት ጠንካራ ኃይል ሆኖ መውጣት አለመቻሉ ብዙ ዜጎችን ‹‹ለውጥ አይመጣም›› ብለው በተስፋ መቁረጥ ውስጥ እንዲገቡ ሲያደርግ፣ ብዙዎችን ለውጡን በገኸው ግንባር አባል ድርጅቶችና አመራሮች ውስጥ ከሚፈጠር ክፍፍል እንዲጠብቁ አድርጓቸዋል። በአገራችን በተቃዋሚ ፓርቲዎች ትግል የፖለቲካ ለውጥ ይመጣል የሚለው ሕዝብ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነ የመጣ ይመስላል። ሕዝቡ አምባገነኑን ኃይል ባይወደውም በተፈጠረው ምስቅልቅል ምክንያት የአፈና ሥርዓቱን ለመሸከም ተገዷል።

የገባንበትን አረንቋ ለመረዳትና መፍትሔ ለመሻት በሳል ውይይት ያስፈልጋል።



# "በአውሮፓ አይሁድ በተገኘበት ሲገደል ግብጽ ውስጥ ሚኒስትር ሆኖ ይሾም ነበር"

## አምባሳደር አቡባከር ኸፍኒ ማህሙድ

**የወቅቱ የኢትዮ-ግብጽ የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ይዞታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ቢገልጹልን?**

ሦስት ዋና ዋና ግቦችን ይዤ ነው ወደ ኢትዮጵያ የመጣሁት:: የመጀመሪያው የሁለቱን አገሮች ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለማጠናከር በሁለቱም አገሮች መካከል መተማመን እንዲፈጠር መጣር ነው:: እንዴት መተማመን ይፈጠራል? ካልን ብዙ መንገዶች አሉን:: አንደኛው የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱን ማሳደግ ነው:: ይኼ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው:: እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንና የግብጽ ኮፕቲክ ቤተክርስቲያን እህት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው:: በሁለቱ ቤተ ክርስቲያናት መካከል በጣም ትልቅ መከባበርና ፍቅር አለ:: በመካከላቸው የማውቀውም የማላውቀው ብዙ ግንኙነት እንዳላቸው አምናለሁ:: የግንኙነቱ ደረጃ ቅዱስነታቸው አቡነ ማትያስ ግብጽን በጎበኙበት ጊዜ እንዲሁም ብጹዕ አቡነ ታዎድሮስ ሁለተኛም ኢትዮጵያ በጎበኙበት ወቅት በሚገባ ታይቷል:: እንዳያችሁት አቡነ ታዎድሮስ ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት የነበረው አቀባበል እጅግ ያማረ ነበር:: በመስቀል በዓል ላይ የነበረው ሥነ ሥርዓትና አቀባበልም እጅግ ውብ ነበር:: እኔም ከአቡነ ታዎድሮስን ጋር ወደ ላሊበላ፣ አክሱምና ጎንደር ሂጄ ስለነበር የሁለቱን እህት አብያተክርስቲያናት መልካም ግንኙነት በመጠኑም ቢሆን ለመገንዘብ ችያለሁ::

በሌላ በኩል በቤተ ክርስቲያናት መካከል እንዳለው ሁሉ በኢትዮጵያና በግብጽ እስላሞች መካከልም ወንድማማችነት አለ:: ስለሆነም በቤተ ክርስቲያናቱ መካከል እንዳለው ሁሉ በዚህም በኩል ተቋማዊ ግንኙነት እንዲኖር ጥረት እያደረግን ነው::

ሁለተኛው የፐብሊክ የዲፕሎማሲ ሥራ ነው:: ከኢትዮጵያ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ቡድን ጋር ጥሩ ግንኙነት አለኝ:: ዶክተሮች፣ አትሌቶች፣ ፓይሌቶች፣ መሐንዲሶች፣ አምባሳደሮች፣ የቀድሞ አምባሳደሮች ሁሉ ያሉበት ጠንካራ ስብስብ ነው:: የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱን በሚገባ እየሄዱበት ነው::

ሦስተኛው ኢንቨርስትመንትን የሚመለከት ሲሆን፣ በዚህም ዘርፍ ጠንክረን እየሠራን እንገኛለን:: ኢትዮጵያ ውስጥ የግብጽ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት 700 ሚሊዮን ዶላር ደርሷል:: በ2015 ግማሽ ዓመት ብቻ 85 ሚሊዮን ዶላር ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ ተደርጓል:: ይህም 30 በመቶ ነው እየጨመረ ያለው ማለት ነው:: ባለፈው ዓመት 65 ሚሊዮን ዶላር ነበር የነበረው:: በፊት ምንም አልነበረም:: ከዜሮ ተነስተን ነው እዚህ የደረስነው:: የተጨበጠ ነገር መሥራት የተጀመረው እ.ኤ.አ. ከ2012 ወዲህ ነው::

ሌላው የስትራቴጂና የደህንነት ጉዳይን የሚመለከተው ዘርፍ ነው:: ስትራቴጅያዊ ግንኙነታችንን ለማጠናከርና ደህንነታችን ለማስጠበቅ በጋራ መሥራት ይጠበቅብናል:: በደህንነት በኩል አሸባሪነትን አብረን እንዋጋለን:: አሸባሪነት አገርም ሃይማኖትም የለውም:: በኬንያ፣ በወታደሮቻችን ላይ በሲናይ፣ በፓሪስም፣ በቤሩትም፣ በባግዳድም፣ በሊቢያም የተፈጠረውን እናውቃለን:: የግብጽንም የኢትዮጵያንም ዜጎች በሊቢያ ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ መቀላታቸውን አይተናል:: እነዚህን ጨካኝ ፍጡራን በጋራ መከላከል አለብን::

**በየመን ስላለው ቀውስና በዚህ ቀውስ ላይ የግብጽ አቋም ምን እንደሆነ እንዲሁም ቀውሱ በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ላይ ሲኖረው ስለሚችለው ተጽዕኖ ቢያብራሩልን?**

የመን በአስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ትገኛለች፤ መጥፎ ጊዜ ውስጥ ገብታለች:: ግብጽ የዐረብ ሊግ አባል አገር

> ግብጽ በአህጉሩ ዴሞክራሲ የሌለባት አገር አይደለችም ከማንም በፊት ዴሞክራቲክ የነበረች አገር ነች

እንደመሆኗ መጠን ለየመን መረጋጋትና ለሕዝቡ ሰላም ትሠራለች:: በየመን ወታደራዊ ኃይል ብቻ መፍትሔ አይሆንም:: ወታደራዊ ኃይሉ ለማረጋጋት ብቻ ነው የሚጠቅመው:: ቀውሱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይቆማል ብለን ተስፋ እናደርጋለን::

**የየመን ጦርነት የሳውዲ ዐረቢያና የኢራን የእጅ አዙር ጦርነት ነው ሚሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች አሉ። የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው? የመን የገባው ሳውዲ መራሹ ጦርስ በዚያች አገር መረጋጋት የሚያመጣ ይመስልዎታል?**

የየመንን ጉዳይ እየተከታተለ ያለው የዐረብ ሊግ ነው:: እንደሚታወቀው በየመን ሕጋዊው መንግሥት በወታደራዊ ኃይል መፈንቅለ መንግሥት ተወግዷል:: በዚህ ምክንያት ነው ብዙ አገሮች ከሳውዲ ዐረቢያ ጋር የተባበሩት፣ ወደየመን ጦራቸውን ያሰማሩትና ሂደቱን የሚደግፉት:: የየመንን ፕሬዝዳንት ሥልጣን ለመመለስ ነው ጥረቱ:: ይህ ከሆነ ፓለቲካዊ መረጋጋት ይኖራል:: ከዚህ ውጪ ጦርነቱ ከኢራን ጋር ለተባለው በበኩሌ እንደዚያ ነው ብየ አላስብም::

**ወደ አፍሪካ ቀንድ እንመለስና ስለሶማሊያና ደቡብ ሱዳን አንዳንድ ነገሮችን እናንሳ። እንደሚያውቁት ሶማሊያ ከሁለት ዐሥርት ዓመታት በላይ ለሚሆን ጊዜ በቀውስ ውስጥ ትገኛለች። በቅርቡ ነጻነቷን ያወጀችው ደቡብ ሱዳንም የሶማሊያን መንገድ እየተከተለች ይመስላል። ግብጽ እንደ አንድ አፍሪካዊት አገር የሁለቱን አገሮች ቀውስ ያላት አቋም ምንድነው?**

የደቡብ ሱዳንን ችግር በተመለከተ በቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ታቦ ኢምቤኪ የሚመራው የሽማግሌዎች ቡድን እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ በጉዳዩ ላይ እየመከረ ነው:: በጁባም በቅርቡ የኢጋድ አባል አገሮች ይመክራሉ:: እነዚህን ሂደቶች እናግዛለን:: ግብጽ የጸጥታው ምክር ቤት አባል ስለሆነች በዚህ በኩል በጣም ታግዛለች:: የሠላም ማስከበሩን የሚደግፉ መኮንኖች በደቡብ ሱዳንም፣ በዳርፉርም፣ በሶማሊያም አሉን:: ግብጽ በሰላም ማስከበሩ ሂደት ቀዳሚ ከሆኑ አገሮች አንዷ ናት::

ከሶማሊያ የሚመጣውን የሽብር አደጋ ለመቀነስ የኢትዮጵያን በሶማሊያ የምታደርገውን እንቅስቃሴ እንደግፋለን:: እኛም ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በሊቢያ ሲገደሉብን ተመሳሳይ ነገር ነው ያደረግነው:: የሰላምና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና መምጣት በሶማሊያ ያለውን ችግር ይፈተዋል ብለን እናምናለን፤ ለዚህም ጠንክረን እየሠራን ነው:: ከዚኸው ጋር በተያያዘ ቀጠናችን የሚያምሰውን አደገኛ አስተሳሰብ መታገል አለብን::

**በቅርቡ በግብጽ የተከሰከሰውንና የብዙ ሰዎች ሕይወት የጠፋበትን የሩሲያ አውሮፕላን አሸባሪዎች ሳይመቱት እንዳልቀሩ የብሪታኒያውን ጠቅላይ ሚኒስትር ጨምሮ ብዙ ሰዎች እየገለጹ ነው። የሩሲያው ፕሬዚዳንት ቭላዲሚር ፑቲንም ሽብርተኞችን ከገቡበት ገብተን እንበቀላቸዋለን ሲሉ መናገራቸው ተሰምቷል። እስኪ ስለጉዳዩ ይግለጹልን?**

ይኼ የምዕራባውያን ጥሩ ያልሆነ ባህል ነው:: እኛ መረጃ ሳይኖረን ፍርድ ውስጥ አንገባም:: ሳይጣራ ምንም ዓይነት መረጃ ልሰጥህ አልችልም:: ከአውሮፓውያንም፣ ከጋራ ብልጽግና አገሮችም፣ ከራሽያም ሁኔታ የተማርነው ብዙ ነገር አለ:: አሁን ከብዙ አገሮች የተውጣጡ የመርማሪ ቡድን አባላት ጉዳዩ ላይ የማጣራት ሥራ በመሥራት ላይ ናቸው:: የመርማሪ ቡድኑ አባላት አውሮፕላኑን ከሠራው ድርጅት፣ ከፈረንሳይ፣ ከራሽያና ከሌሎችም ብዙ አገሮች የተወጣጡ ናቸው:: ‹‹ብላክ ቦክሱ›› ለምርመራ ወደ አውሮፓ ሄዷል:: የምርመራው ሪፖርት ከመውጣቱ በፊት ልነግርህ የምችለው ምንም ነገር የለም:: ውጤቱን ከመጠበቅ ውጭ እኔ አስማተኛ አይደለሁምና እንዲህ ነው ልልህ አልችልም::

**አሁንም ግብጽ ውስጥ እንቆይ። ከአራት ዓመት በፊት የተካሄደው የግብጽ አብዮት በብዙዎች ዘንድ ከፍተኛ ተስፋ የፈነጠ እንደነበር ይታወቃል። ይሁን እንጂ በሚያሳዝን ሁኔታ አብዮቱ አልተሳካም። ብዙዎች ከአብዮቱ መቀልበስ በኋላ የግብጽ የዴሞክራሲ ጅማር ተሸመድምዷል ይላሉ። እርስዎ ሁኔታውን እንዴት ነው የሚገልጹት?**

ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ ነው የሮጥከው:: አብዮቱ

ወደ ገፅ 7 ዞሯል



## ነጻ አስተያየት

አክሎግ ቢራራ (ዶ/ር)

# እድገቱ ለማን ነው?

## አዲስ ትርጉም የሚያስፈልገው የልማት መርህ

ባለፉት ዐሥር ዓመታት፤ ማለትም፤ ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ፤ ኢትዮጵያ ፈጣን እድገት እንዳሳየች እቀበላለሁ። የፈጣን እድገቱ ትኩረት መንግሥት ባካሄደው በመሠረተ ልማት -መንገዶች፤ ድልድዮች፤ ትምህርት ቤቶች፤ የጤና ጣቢያዎች፤ የመሰብሰቢያ አዳራሾች፤ የመብራት ኃይል ማመንጫ ግድቦች፤ የሃዲድ መንገዶች፤ ፎቆች፤ ቪላዎችና ከዚህ ጋር የተያያዙ ከተሞች ወዘተ. ከመስፋፋት ላይ ነው። አገሪቱ ዘመናዊ እድገቷን ከዝቅተኛ ደረጃ ላይ ስለጀመረች እድገቱ ግዙፍ እንደሚመስል አይካድም። ‹‹አስደናቂው›› እድገት በተከታታይ የተካሄደው ከምርጫ ዘጠና ሰባት ወዲህ ነው። አንደኛው የማስተናግደው ጥያቄ ኢትዮጵያ ይኼን እድገት ምን ግብዓት አግኝታ ስኬታማ ለማድረግ ቻለች? የሚለው ነው። ሁለተኛውና ቁልፉ ጥያቄ የእድገቱ ውጤት ዋና ተጠቃሚ ማነው? የሚል ነው። መልካም አስተዳደር ነጻነትን፣ ፍትሕን፣ የሕግ የበላይነትን፣ ግልጽነትን፣ ተጠያቂነትን፣ ተሳታፊነትን ወዘተ. የሚያካትት የመንግሥት ሥርዓትና የአስተዳደር ጥያቄ ነው። ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የእድገቱ ውጤት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት መልካም አስተዳደር ሲኖር ነው ተብሎ የሚተቸው በዚህ ምክንያት ነው።

ከቀድሞዎቹ የኢትዮጵያ መንግሥታት ጋር ሲነጻጸር በትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጭ ግንባር (ሕወሓት) ብቸኛ የፖለቲካ የበላይነት ለሚያሽከረክረው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሳዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) መንግሥት በኢትዮጵያ ረዢም ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ እርዳታ የምዕራብ መንግሥታትና የሚቆጣጠሯቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለግሰዋል። ስደተኛውም ወገኑን ለመርዳትና የራሱን ኑሮ ለማሻሻል የለገሰውና ያፈሰሰው መዋዕለንዋይ የሚናቅ አይደለም። ስለሆነም በኢትዮጵያ እድገትና እየጨመረ በሄደው የውጭ ለልማት ይውላል ተብሎ በተሰጠው እርዳታ መካከል ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እናያለን።

በ1997/1998 $675 ሚሊዮን የነበረው ለልማት የተሰጠ እርዳታ በ2006 ወደ $1.9 ቢሊዮን፤ በ 2012 ወደ $4 ቢሊዮን፤ ከዚያ ወዲህ ያለው በዓመት በዝቅተኛ $4 ቢሊየን ደርሷል። ስለዚህ በመሠረተ ልማት የሚታይ፤ የሚዳሰስ እድገት ባይኖር አከራካሪ ይሆን ነበር እላለሁ። ገዢው ፓርቲ የሚታይ መሠረተ ልማት ስኬታማ ባያደርግ እርዳታው እየጨመረ አይሄድም ነበር። በአብዛኛው ለልማት አስፈላጊ የሆነው መሠረተ ልማት እየተስፋፋ ሲሄድ አብሮ የሚራመደው መዋቅራዊ ለውጥና የኅብረተሰቡ ኑሮ መሠረት ይይዛል። በዋናው መስፈርት ሳየው፤ የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ እየተሻሻለ ይሄዳል፤ ሕዝቡ በመንግሥት መሪዎች ላይ እምነት ይኖረዋል፤ ከተፈጥሮ የሚመጣን ረኀብ ለመቋቋም ይቻላል፤ ገቢ እያደገ ስለሚሄድ መንግሥት ከታክስና ከሌላ የሚያገኘው ገቢ እያደገ ይሄዳል፤ በውጭ አበዳሪዎች፤ መንግሥታትና ለጋሶች የሚኖረው ጥገኝነት እየቀነሰ ይሄዳል። ከአገር እየሸሸ የሚሄደው የወጣቱ ትውልድ ቁጥር እየቀነሰ ይሄዳል፤ ከተፈጥሮ የሚከሰት ረኀብተኛ ቁጥር እየቀነሰ ይሄዳል ወዘተ። ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ ጠንካራ ሆኖ የአገሪቱ የምርት ውጤት እየጨመረ ሲሄድ ከድርቅ የሚከሰትን ረኀብ ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ይቻላል። ይኼ የማይካድ ሁኔታ ከቀጠለ ኢትዮጵያ የቱኒዚያና ሌሎች የዐረብ አገሮች የደረሰባቸው ሁኔታ ይደርስባታል። ኪራይ ሰብሳቢነት፤ የቡድንና ሌላ አድልዎ፤ ሙስና፤ የአስተዳደር በደል፤ የሰብአዊ መብቶች መገፈፍ ወዘተ. መንግሥታትን እንደሚያንበረክክ የሚያከራክር አይመስለኝም።

የመሠረተ ልማት መስፋፋት እንዳለ ሆኖ፤ በዚህ ትችት የማቀርበው ክርክርና ትንተና ባለፉት ሃያ አራት ዓመታት በሕወሓት ብቸኛ የበላይነት የሚመራው የኢሕአዴግ ‹‹ልማታዊ መንግሥት›› አስገኘሁት

> የኢትዮጵያ የመንግሥት ጠባብና ጎሰኛ በሆኑ ክፍሎች መማረኩ ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተመጣጣኝ ተሳትፎና የእድገት ውጤት ተጠቃሚነት ማነቆ ሆኗል

የሚለው ‹‹አስደናቂ›› የእድገት ውጤት ለጥቂት ደላላዎች፤ ነጋዴዎችና የወፍ ዘራሽ ሀብታሞች ከፍተኛ ገቢና ሀብት አስገኝቷል፤ ጎሳዊ አድልዎን፤ የአስተዳደር ብልሽትን፤ የተዛባ ገቢንና እድገትን፤ ኪራይ ሰብሳቢነትን፤ ድርጅታዊ ምዝበራን፤ ሙስናንና ከሕግ ውጭ ከአገር የሚሸሸውን ሀብት መጠን ወደ አደገኛ ደረጃ አሸጋግሮታል የሚል ነው።

በተጨማሪም የኢትዮጵያ የመንግሥት ጠባብና ጎሰኛ በሆኑ ክፍሎች መማረኩ ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተመጣጣኝ ተሳትፎና የእድገት ውጤት ተጠቃሚነት ማነቆ ሆኗል። የምከራከረው ኢትዮጵያ እንደ አገር ያላትን የተፈጥሮና የማኀበረሰብ ጥሪቶች፤ የውጭ እርዳታ፤ ከስደተኛው የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬና ሌላ ግብዓት ሙሉ በቡሉ ተጠቅማ የሥራ፤ የገቢ እድገትና የሀብት ክምችት ዕድል ለሁሉም ዜጎቿ ለማቅረብና የምርት ውጤቶቿን ለመጨመረ የምትችለው ሁሉም ዜጎች የሚሳተፉበትና ጥቅም የሚያገኙበት የእድገት መርህ መሠረት ሲይዝና የሕግ ዋስትና ሲኖረው ነው። ሕዝብን የእድገቱ ማዕከል ያደረገ አገዛዝ ከሕዝቡ የሚፈራው ነገር የለም፤ ያላደረገ አገዛዝ ደግሞ ዞሮ ዞሮ ጊዜ ቢወስድም በሕዝብ ቁጣና እምቢተኛነት ይንበረከካል። ኢትዮጵያ ታላቅ አገር እንድትሆን፤ መላው ሕዝቧ ከአስቃቂ ድህነትና ኋላ ቀርነት ዑደት ነጻ ወጥቶ ጤናማ ኑሮ እንዲኖር ጥረት ማድረግ የሁላችንም ኃላፊነት ነው። በእኔ ግምት በጎ ፈቃደኛነት ካለ ይኼ ይቻላል። ይኼን ታሪካዊ ኃላፊነት ለመወጣት የምንችለው ተቃዋሚው፤ መላው የማኅበረሰብ ክፍልና ገዢው ፓርቲ አብረው የሚሠሩበት የፖለቲካ ሁኔታ ተመቻችቶ ሁሉን አቀፍ፤ ፍትሐዊ፤ አሳታፊ፤ ሰላማዊና ዴሞክራሳዊ የሆነ አገዛዝ እንዲመሠረት የጋራ ጥረት ማድረግ ነው። በርማ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናት። ጋናም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናት።

### ተግዳሮቶቹ የሥርዓት ናቸው፤ የግለሰብ አይደሉም

ሰሞኑን በአገር ቤትና በውጭ ኢትዮጵያዊያንን የሚያነጋግረው አስኳል ጉዳይ በጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ የሚመራው ኢሕአዴግ በራሱ ፈቃድ ሞያተኞችን ተጠቅሞ ስለ መልካም አስተዳደር ያደረገው ሰፊና ጥልቀት ያለው ጥናት፤ ግኝትና ውይይት ነው። ይኼ ከዚህ በፊት ያልታሰበና ያልታየ ብሔራዊ ጥናትና ምርምር አሁን ለምን ተደረገ? የሚለው ጥያቄ አግባብ ቢኖረውም እኔ ለጥያቄው መልስ ለመስጠት አልፈልግም፤ አልሞክርም። ቁም ነገሩ ባለሞያዎቹ መሠረታዊ ተግዳሮቶችን መርጠው በሦስት ወራት የሰበሰቡት መረጃ፤ ያነጋገሩት የኅብረተሰብ ስርጭት አግባብነት፤ ያቀረቧቸው ግኝቶች እጅግ በጣም አስደናቂና የሕዝብን ብሶት

ወደ ገፅ 10 ዞሯል



ኤርሚያስ ለገሰ

# ረኀቡና ኢሕአዴጋዊ እውነታዎች

ሕወሓት መራሹ መንግሥት በኢትዮጵያ ውስጥ ረኀብ በተከሰተ ቁጥር የረኀቡን ዋነኛ ምንጭ ‹‹የአየር ንብረት መዛባት›› በሚል ውጫዊ ምክንያት ማላከኩ የተለመደ ሆኗል። ለአብነት ያህል የዛሬ ዘጠኝ ዓመት በኢትዮጵያ ረኀብ በተነሳ ወቅት ‹‹የሰሞኑ የረኀብ ፖለቲካ›› በሚል ርእስ የውስጥ ድርጅት ሰነድ ተዘጋጅቶ ነበር፤ ደራሲው ኀድ መለስ ዜናዊ ነበር። በማስከተልም የፓርቲው ከፍተኛ ካድሬዎችና የመንግሥት ባለሥልጣናት ውይይት እንዲያደርጉበት ተደረገ። በዚህ ሰነድ ገጽ 6 ላይ የረኀቡን ዋነኛ ምንጭ እንደሚከተለው ይገልጻል፡-

‹‹ረኀቡ ከምን እንደሚመነጭ በትክክል ማስቀመጥ መፍትሔውን ለማስቀመጥ ወሳኝ ነው። የረኀቡ ቀጥተኛ ምንጭ ከአየር ንብረት መዛባት ጋር ተያይዞ የተከሰተው ድርቅ ነው። የአየር ንብረቱ መዛባትና ድርቁ እኛ ያልፈጠርነው ልናስተካክለው የማንችለው ነባራዊ ሃቅ ነው። በዚህ ነባራዊ ሁኔታ ማዕቀፍ ድርቁን ተቋቁመን ረኀቡን ለማስወገድ ያስቀመጥነው ስትራቴጂ ተዓምር ሠሪነቱ በንድፈ ሐሳብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በተግባር ተረጋግጧል። የረኀቡ ዋነኛ ምንጭም የአየር ንብረት መዛባትና ድርቅ ነባራዊ ሁኔታን መቋቋም ረኀብን ለማጥፋት የቀየስነው ስትራቴጂ በሚፈለገው ፍጥነት በሁሉም አካባቢዎችን ስላልተፈጸመ ነው።››

እስኪ ይታያችሁ! ዛሬ ዘጠኝ ዓመት በፊት (በ1999 ዓ.ም.) የድርቁ መንስኤ የአየር ንብረት መዛባት እንደሆነ ተነገረን። ከዚያ በፊትም ምንጩ ተመሳሳይ ነበር። አሁንማ ልማድ ሆኖብን በኢትዮጵያ ምድር በየሁለት ዓመቱ ረኀብ የሚከሰት ሲሆን ምንጩ የአየር ንብረት ለውጥ ሆኗል። በነገራችን ላይ በአገራችን ላይ በተጠቀሰው ዓመት ድርቁ ወደረኀብ በመቀየሩ ምክንያት በርካታ ሕጻናትና እናቶች ሞተዋል። በአራቱም ማዕዘናት ዜጎች ቀያቸውን ለቀው ተሰደዋል። የተፈጠረው አስደንጋጭ ሁኔታ ከሕሊና የሚጠፋ አልነበረም።

በዚያ ወቅት ‹‹በምጥቁ መሪ!›› አብዮታዊ አመራር ሰጪነት የተሠራው ወንጀል ዘመን ተሻጋሪና ነገ ከነገ ወዲያ ተጠያቂነትን የሚያመጣ ነው። እንዲህ ነበር የሆነው፡- በኢትዮጵያ ሚሊኒየም ዋዜማ የተከሰተው ድርቅ ወደረኀብ መሸጋገሩን የሚያሳይ ሪፖርቶች ከመላው አገሪቱ መሰማት ጀመሩ። የኢሕአዴግ የፕሮፓጋንዳ ማሽን ከዚያ ዓመት በፊት በነበሩት አራት ዓመታት ኢኮኖሚያችን በሁለት አሃዝ አድጓል፤ ሚሊየነር አርሶ አደሮች መፍጠር ችለናል ወዘተ. በሚል ቅኝት የሚመራ ስለነበረ ይህን መርዶ ለመቀበል አስቸጋሪ ሆነ። ረኀብን አስወግደናል ብለን ባወጅን ማግስት በረኀብ ተጠቅተን መገኘት በእርግጥም አሳፋሪ ነበር። የአመራርና የማስፈጸም አቅማችን፣ ምርጥ ልምዶች የማስፋት ስትራቴጂያችን ለዓለም ተምሳሌት ሆኗል ባልን ጥቂት ቀናት ውስጥ ሕዝቡ ረኀቡን መቋቋም አቅቶት እየተሰደደ መሆኑ መመልከት ፕሮፓጋንዳችን ‹‹ቢወቅጡት እምቦጭ›› እንደሆነ የሚያመላክት ሆነ።

እንደተፈራው በሚሊኒየሙ ዋዜማ የሰው ሕይወት በየቦታው መውደቅ ጀመረ፤ ረኀቡን መቋቋም የማንችልበት ሁኔታ ግልጽ ሆኖ ወጣ። የመጀመሪያ ሰሞን እውነታውን አውገርግሮ ከማቅረብ ይልቅ ትክክለኛው መረጃ ተሰብስቦ ወደኢሕአዴግ ቢሮ እንዲመጣ ልዩ ውሳኔ ተላለፈ። ለማመን በሚቸግር ሁኔታ የረኀቡ ዋነኛ ሰለባ ከሆኑት አካባቢዎች የሚመጣው መረጃ እጅግ አስፈሪና አስደንጋጭ ሆነ። ከሶማሊያ ጫፍ እስከ አብርሃ አጽብሃ የሚባል የትግራይ ቀበሌ ድረስ ሕዝቡ የሚላስ የሚቀመስ ማጣቱ ታወቀ። የከፋ ረኀብ ያጋጠማቸው አካባቢዎች ልጆቻቸውን እየቀበሩ ቀያቸውን እየለቀቁ መሰደድ መጀመራቸው እሙን ሆነ።

በሚሊኒየሙ ዋዜማ የችጋሩ ዋነኛ ተጠቂ ከሆኑት አካባቢዎች የመጀመሪያው የሱማሌ ክልል ነበር። የሱማሌ ክልል ኢሕአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ ጀምሮ ለሥርዓቱ ተገዢ እንዳልሆነ በገሃድ የሚታወቅ እውነታ ነው። በዛ ላይ አካባቢው በጦርነት የሚታመስ መሆኑ የረኀብ አደጋው በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ አደረገው። በወቅቱ የተፈጠረው ረኀብ በ10ሺዎች የሚጠጉ የቀንድና የጋማ ከብቶች መሞታቸው ታወቀ። ከ80 እስከ 100 የሚሆኑ ሕጻናት በረኀቡ ምክንያት ሕይወታቸው እንዳለፈ የሚያሳይ መረጃ የስም ዝርዝር ሪፖርት ቀረበ።

ይህንን የሱማሊ ክልል የረኀብ ሁኔታ የተቀበለው ኀድ በረከት ከ‹‹ባለራዕዩ መሪ›› ጋር በመነጋገር አንድ ጠንካራ ትእዛዝ ሰጠ። ጥብቁ ትእዛዝ ‹‹ማንኛውም የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ጋዜጠኛ፣ በመንግስት ክትትል የማይደረግበት በጎ አድርጎት ድርጅት ወደሶማሊያ ዝር እንዳይል!›› የሚል ነበር። እነሆ ላለፉት 10 ዓመታት የትኛውም የነጻ ፕሬስ ሆነ የውጭ ጋዜጠኛ ወደሶማሊ ክልል ልሂድ ብሎ ጥያቄ ቢያቀርብ አይፈቀድለትም። ከኀድ በረከት ጋር የቅርብ ወዳጅነት የመሠረቱትም ቢሆን ፈቃድ አያገኙም። የተለያዩ ምክንያቶች እየተሰጣቸው ጥያቄዎች እንዲጥሉ ይደረጋል። በዚህ ምክንያት በሱማሊ ክልል በረኀቡ የሞቱት ሕጻናት ከሪፖርቱ ውጪ እንዲሆኑ ተደረገ። እስከ 100 የሚደርሱት ሕይወታቸው ያለፉት ሕጻናት ማህደር በኢሕአዴግ ቢሮ ተቆለፈበት።

በሚሊኒየሙ ዋዜማ ሌላኛው የረኀቡ ተጠቂ አካባቢ ደቡብ ኢትዮጵያ ነበር። ረኀብ ታሪክ ተደርጎበታል በተባለው ደቡብ ኢትዮጵያ ወስጥ ሚሊዮኖች እየረገፉ መሆኑን አስቀድመው መረጃ የመጡት መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የውጭ ጋዜጠኞች በመሆናቸው መደበቅ የሚቻል አልነበረም። ከዚህም በተጨማሪ የውጭ ጋዜጠኞች የተፈናቀሉና የሞቱ ሰዎች የሚያሳዩት ዘገባዎችን ለዓለም ሕዝብ በማስተላለፋቸው ምክንያት መነጋገሪያነቱ ከጫፍ ጫፍ ናኘ። በመሆኑም ነባራዊ ሁኔታውን እንደቅቡል መውሰድ፣ ግን ደግሞ እውነታውን አውገርግሮ ማቅረብ የአቶ መለስ መራሹ የመንግሥት የፕሮፓጋንዳ ስትራቴጂ ሆኖ እንዲቀረጽ ተደረገ።

በዚህም ምክንያት የተራበው ሕዝብ ከ14 ሚሊዮን በላይ ቢሆንም ኀድ መለስ ባዘጋጀው ‹‹የሰሞኑ የረኀብ ፖለቲካ›› የውስጠ-ድርጅት ሰነድ ጨምሮ የመንግሥት ሚዲያ ተቋማት 6.4 ሚሊዮን ብቻ ለረኀብ አደጋ መጋለጣቸው አሳወቀ። በሱማሊ፣ በአፋር፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ከ500 ያላነሱ ሕጻናት በረኀብ ቢሞቱም የፕሮፓጋንዳ ማሽን ከ30 እንደማይበልጡ

ወደ ገፅ 8 ዞሯል

## ነጻ አስተያየት



መስከረም አበራ

# ደንጋራው ብአዴን
## ፪

### ሕዝብ አልቦው ብአዴን

በ1968ቱ ማኒፌስቶው ‹‹የአማራ ብሔር ጨቋኝ ናት›› ሲል በደፈናው አማራን ሁሉ ፈርጆ ከተነሳው ሕወሓት ጋር ግንባር ገጥሞ አዲስ አበባ የገባው ኢሕዴን ውሎ አድሮ ‹‹የአማራ ጭቁን ሕዝብ ወኪል ነኝ፣ ስሜም ብአዴን ነው›› ብሏል:: ለነገሩ ሕወሓትም መጠነኛ ስክነት ሲያገኝ ቢያንስ በቃል ሁሉም አማራ ጨቋኝ አይደለም ማለት ጀምሯል:: ሆኖም የትኛው አማራ ነው ጨቋኙ በሚለው ላይ በሕወሓት/ኢሕአዴግ መንደር ስክነት የለም:: አቶ መለስ ‹‹ጨቋኙ የሸዋ አማራ ነው›› ሲሉ እነ አቶ በረከት ደግሞ ‹‹ጨቋኙ የአማራ ገዥ መደብ ነው›› ይላሉ:: ለመሆኑ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ታሪክ ውስጥ ገዥ ሆኖ ያልጨቆነ ዘር ይገኝ ይሆን? አገዛዝና ጭቆናስ በአገራችን ዘር ለይተው የሚገናኙ ጉዳዮች ናቸው? ወይስ ሥልጣን ሲያገኝ ጫቋኝ የሚሆነው አማራ ብቻ ነው? አማራ ያልሆኑቱ፣ በኢትዮጵያ የገዥነት ሥልጣን እርከን ላይ የነበሩ ሰዎች ያስተዳድሩ የነበረው ከጭቆና በራቀ ዴሞክራሲያዊ ዘይቤ ነበር?

ይህ ማለት የመጨረሻው ዘውዳዊ አገዛዝ ማገር የነበሩት እነ አቶ ይልማ ደሬሳ፣ የደርጉ ባለሚሎች እነ ጓድ ተስፋዬ ዲንቃ፣ ደበላ ዴንሳ፣ ጴጥሮስ ገብሬ፣ ተስፋዬ ወልደሥላሴ፣ ፍሰሐ ደስታ ወዘተ. አማሮች ባለመሆናቸው ከጨቋኝነቱ ማኅበር የሉበትም ማለት ነው! ወይስ እነዚህ ሰዎች በገዥው መደብ ውስጥ ተሰግስገው ያሳዩት የጭቆና ማኅበርተኝነት ሃጢያት አማራ ባለመሆናቸው ብቻ ይሰረይላቸውና የጨቋኝነቱን መርገም ሁሉ አማራ ጓዶቻቸው ይወስዳሉ? እንደ ባለአእምሮ ለሚያስብ በጨቋኞች ወንበር የተቀመጠ ቀርቶ ጭቆናን እያየ ያልተቃወመ ሁሉ የሞራል ፍርደኛ ነው:: በተቀረ ጭቆናን በዘር የሚተላለፍ መርገም አድርጎ አንድን ዘር ማብጠልጠል የበታችነት ከሚያሰቃየው ልቦና የመነጨ ራስን የማስገመት አካሄድ ነው::

እንዲህ ለፍረጃ በቸኮለ ሁኔታ አማራውን ሰድበው ለሳዳቢ፣ አድነው ለአዳኝ ወጥመድ ሲሰጡ የኖሩት ሕወሓት/ኢሕአዴጎች ናቸው እንግዲህ ከዕለታት አንድ ቀን ኢሕዴን ወደ ብአዴን አንሶ ለጭቁኑ አማራ መቆም አለበት ሲሉ ብአዴንን ያነጎቱት:: የብአዴን ለአማራው ሕዝብ እውነት መቆም አለመቆም ተጠየቅ ብዙ የሚያከራክረውም በዚሁ ምክንያት ነው:: ከዚህ ጋር መነሳት ያለበት ጉዳይ ለብዙ ዓመታት በተጻፉ መዛግብት ሳይቀር በጨቋኝነት ሲብጠለጠል የኖረው የአማራ ሕዝብ እንዴት ነው ነጻ አውጭ ፓርቲ ያስፈለገው የሚለው ነው:: ይህችን ለማለባበስ ነው በአማራው ሕዝብ ላይ ብዙ ግፍ ከተሠራ በኂላ (ከአርባጉጉው፣ ከበደኖው … ዋይታ በኂላ) ሕወሓት/ኢሕአዴግ የአማራው አርሶ አደርና የአማራው ገዥ መደብ ተለያይቶ መታየት አለበት እያለ ያለው:: ይህ አባባሉ ቢረጋለትም ሕወሓት/ኢሕአዴግ ስህተቱን አረመ ብሎ መቀበል ይቻል ነበር:: ግን ይህም አልሰነበተለትም:: እንጀራ ፍለጋ ወደ አገሩ ሌላ አካባቢ ሰርቶ ለመኖር የሄደውን ደሃ አርሶ አደር ‹‹ሞፈር ዘመት›› የሚል ስም ተለጥፎለት እንዲፈናቀል ሲደረግ አይተናልና በኢሕአዴግ ዘንድ የአማራ ገዥ መደብ ከአማራ አርሶ አደር ተለይቶ ታይቷል ብንባል እንዴት እናምናለን:: ለአማራ ጭቁን አርሶ አደር ብቻ ቆሜያለሁ የሚለው ብአዴን ይህን በተመለከተ አንዳች ነገር ትንፍሽ ያለማለቱ ተልዕኮው ከሚናገረው የአማራ ሕዝብ ጥብቅና ጋር እንደማይገናኝ ያሳብቃል:: ይብስ ብሎ ‹‹የቆምኩት በአማራ ክልል ላለ አማራ ብቻ ነው›› ሲል እያደር ማነሱን አስመሰከረ:: በሕወሓት/ኢሕአዴግ አስተሳሰብ ሎተሪ ሊያዞርም ሆነ የጉልበት ሥራ ሊሠራ ከክልሉ የወጣ አማራ ሁሉ ነፍጠኛ ነውና ብአዴን ደግሞ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ምልምል ነውና የቆመው በክልሉ ረግቶ ለተቀመጠው አማራ ነው፣ ይህም ትክክል ነው እንበል:: ይህን ብለንም ደንጋራው ብአዴን ሌላ ጥያቄ የሚያጭር ነገር ይደቅንብናል:: አሁን በቅርቡ የአማራ ሕዝብን በሚመከት ነውረኛ ንግግር የተናገረው ዓለምነው መኮንን የሚመራው ፓርቲ ለአማራ ሕዝብ ጥቅም ቆሜ አድራለሁ ቢል ለመቀበል ማሞ ቂሎን መሆን አለብን::

### የብአዴን ‹‹የአማራ ብሔረተኝነት››

‹‹ኢቢሲ›› ሰሞኑን የብአዴን ባለሥልጣናት ቀደም ሲል ተናገሩትን ንግግር መልሶ ሲያስደምጥ ሰንብቷል:: እነዚህ ባለሥልጣናት ከሚናገሩት ንግግር መካከል ስለ አማራ ብሔረተኝነት የተናገሩት ትክክለኛውን የብአዴን ተልዕኮ አመላካች ነው:: ከአንገትም ሆነ ከአንጀት ለበአዴን አመራሮች አሁን ያለው የአማራ ሕዝብ ፈለግ ለሁለት ይከፈላል- የአማራ አርሶ አደር እና የአማራ ልሂቃን በሚል:: የአማራ ልሂቃን የተባሉት በአመዛኙ በኢትዮጵያ አንድነት ስም የሌላውን ብሔር ማንነት የመጨፍለቅ ዓላማ ያላቸው የቀድሞ ሥርዓት ናፋቂ ትምክህተኞች የሚባሉት ናቸው:: የአማራው አርሶ አደር ደግሞ እንደሌሎቹ ብሔሮች ተጨቋኝ ነው:: ስለዚህ የአማራው ብሔረተኝነት ትግል መቃኘት ያለበት በተጨቋኙ አርሶ አደር ነው ባይ ናቸው - ብአዴናውያኑ:: እዚህ ላይ ብዙ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል::

እንደሚታወቀው የአገራችን የብሔር ፖለቲካ አጀንዳ የሚቀረጸውም ሆነ የሚዘወረው በየብሔሩ ልሂቃን እንጂ በአርሶ አደሩ አይደለም:: የአማራውን ብሔር ፖለቲካ አጀንዳ ከዚህ ሃቅ የሚለየው ምክንያት የለም:: ስለዚህ የአማራ ልሂቃን የአማራውን ብሔረተኝነት አይቀበሉም የሚለው የብአዴኖች ትንታኔ በሌላ ጎኑ ሲታይ የብአዴን ፖለቲካዊ ማንነትና የትግል ዘይቤ ለአብዛኞቹ የአማራ ልሂቃን የሚዋጥ አይደለም ማለት ነው:: ይህ ማለት ብአዴን ዓላማውን የሚያነሱ ተተኪ የአማራ ልሂቃንን በበቂ ሁኔታ ማፍራት አልቻለም ማለት ነው:: ይህ ደግሞ ከጫካ የመጡት የብአዴን ጉምቱዎች ሲያልፉ በእግራቸው ተተክቶ የፓርቲውን ህልውና ቀጣይ የሚያደርግ ተተኪ እንዲቸግር ያደርጋልና የብአዴንን ቀጣይ ህልውና ፈተና ላይ ይጥለዋል:: ስለዚህ ለብአዴን የሚጠቅመው በሩቅ ሆኖ የአማራውን ልሂቅ ከማውገዝ ይልቅ ልሂቁ ለምን ይርቀናል ብሎ ራስን መፈተሹ ነው::

የብአዴኖች ትንታኔ ሌላው አንጓ የአማራው የብሔረተኝነት ፖለቲካ መቃኘት ያለበት በአርሶ አደሩ ነው የሚለው ነው:: ከላይ እንደተገለጸው የአገራችንን የብሔር ፖለቲካ የሚዘውሩትም ሆነ ከፖለቲካው ቱርፋት ትርፍ የሚሰበስቡት የየብሔሩ ልሂቃን እንጂ አርሶ አደሩ አይደለም:: እራሳቸው ብአዴንን የሚዘውሩት አማራ ነን ባዮቹ የብአዴን ልሂቃንም አርሶ አደሮች አይደሉምና በአባባላቸው መሠረት ሙጥኝ ያሉትን ወንበራቸውን ለአርሶ አደሩ መልቀቅ ነበረባቸው:: በተግባር ግን ይህን እንደማያደርጉ ግልጽ ነው:: ስለዚህ የአማራውን ብሔረተኝነት አርሶ አደሩ ይቃኘው ማለት የማይመስል ትርጉም አልባ ነገር ነው::

### ከርካሚው ብአዴን

የኢሕአዴግ ፖለቲካ ዋና መዘውር የሆነው የብሄር ፖለቲካ ካልተሳኩለት ነገሮች አንዱ የአማራውን ብሔርተኝነት ማምጣት ነው:: ብአዴን በአማራነት ከረጢት ውስጥ ገብተው ኢትዮጵያዊነታቸውን ሁለተኛ የሚያደርጉ የአማራ ልሂቃንን በሰፊው ማየት ይፈልጋል:: አለቃው ሕወሓት የቀድሞው ሥርዓት የአማራን ሁለንተናዊ የበላይነት ለማስፈኑ ከውልደት ፍጥረቱ ጀምሮ የሚያቀነቅነውን ዜማ ለአማራ ሕዝብ ቆሜያለሁ የሚለው ብአዴንም የሚያስተጋባው ነው:: ይህ ሕወሓትን ያደቆነው ሐሳብ ብአዴን ከኢሕዴን ወደ ብአዴን እንዲኮማተር የፈለገበት የሕወሓት ዋና ዓላማ ነው:: ሕወሓት ስለ አማራ ሕዝብ የነበረውን አሁንም የለቀቀው የማይመስለውን አቋም ለመገንዘብ 1968ቱን ማኒፌስቶውን ማንበብ ይጠቅማል::

የሆነ ሆኖ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ብአዴንን የሚፈልገው አማራው ኢትዮጵያዊ ነኝ ሚለውን የሥነ ልቦና ከፍታውን (በሕወሓት አስተሳሰብ የበላይነት ትምክህቱን) ትቶ ወደ ተጨቋኝ አማራነት የጎሳ ጎሬ እንዲገባለት እንዲሰብክለት ነው

የአማራውን ብሔር የቀድሞ ሥርዓት ብቸኛ ማገር አድርጎ የሚያስበው ሕወሓት በቀድሞ ሥርዓቶች ለተሠሩ ጥፋቶች ሁሉ አማራው ኃላፊነትን እንዲወስድ ይሻል:: ብአዴንም በዚህ ይስማማል:: አማራው ለአለፈው ጥፋት ሁሉ ኃላፊነት ወስዶ፣ ሌሎችን ብሔሮች ይቅርታ ጠይቆ ባልሠራው ብቻ ባልነበረበት ዘመን በተሠራ ‹‹ጥፋት›› እየተሸማቀቀ እንዲኖር የሚያደርገውን አካሄድም ብአዴንና ሕወሓት የዴሞክራሲያዊ ብሔረተኝነት ድንቅ አብሮ የመኖር ዘይቤ ሲሉ ያሞካሹታል:: ለዚህ ነው እነ አያሌው ጎበዜ አማራው ከያለበት ሲፈናቀል ጭጭ ያሉት፣ እነ ታምራት ላይኔና ዓለምነው መኮንን የአማራን ሕዝብ ሲሳደቡና ሲያስገድሉ የኖሩት::

ጠቅለል ሲል የአገሪቱን ፖለቲካ የሚዘውረው ሕወሓት ለረዥም ጊዜ ሲጨቁን ነበር ብሎ የሚያስበውን የአማራ ብሔር ከፍተኛ የሥነ ልቦና የበላይነት የተሸከመ ትምክህተኛ አድርጎ ያስበዋል:: ሕወሓት ትምክህት ሲል የሚረዳው በአመዛኙ አማራውን በአማራ ብሔረተኝነት ከረጢት ውስጥ ለመግባት ማስቸገርና ለኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት ማድላቱን ነው:: ይህንን ደግሞ በኢትዮጵያዊነት ሽፋን የቀድሞውን የአማራ የበላይነት በአገሪቱ ለማምጣት የአማራ ልሂቃን የሚያደርጉት ጥረት አድርጎ ይተረጉመዋል - ጠርጣራው ሕወሓት:: ስለዚህም አማራው ከኢትዮጵያዊነት የሥነ ልቦና ከፍታ ወደ ተጨቋኝ አማራነት ዝቅ እንዲል ይፈልጋል:: ለዚህ ነው ሕወሓት በብአዴን አድሮ ‹‹አብዛኛው አማራ እንደሌሎች ብሔረሰቦች በቀድሞው ሥርዓት የተጨቆነ ነው›› የሚል አዲስ ዘፈን ያመጣው:: ይህ ከአንጀት እንዳልሆነ፣ ሕወሓት/ኢሕአዴግ አማራን ሁሉ በአንድ የጨቋኝነት ዓይን እንደሚያይ ጭቁን ነው የሚለውን የአማራ ደሃ አርሶ አደር ከነልጆቹ ያለርህራሄ ሲያፈናቅል አረጋግጧል::

የሆነ ሆኖ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ብአዴንን የሚፈልገው አማራው ኢትዮጵያዊ ነኝ ሚለውን የሥነ ልቦና ከፍታውን (በሕወሓት አስተሳሰብ የበላይነት ትምክህቱን) ትቶ ወደ ተጨቋኝ አማራነት የጎሳ ጎሬ እንዲገባለት እንዲሰብክለት ነው:: ይህ ግን እንደታሰበው የሄደ አይመስልም:: መገለጫው ደግሞ ብአዴን የአማራ ልሂቃንን ‹‹ዴሞክራሲያዊ ብሔረተኝነትን የማይቀበሉ ትምክህተኞች አሉበት›› ሲል መውቀሱ ነው:: ይብስ የሚገርመው ብአዴን ውስጥ ያሉ መካከለኛና ዝቅተኛ አመራሮች ራሳቸው ለብአዴን አካሄድ ባዳነት ማሳየታቸው ነው:: የአቶ ዓለምነውን የቅሌት ንግግር ቀርጸው ለሕዝብ ይፋ ያደረጉት በራሱ በብአዴን ዝግ ስብሰባ የተገኙ ካድሬዎች መሆናቸውን ልብ ይሏል:: በተመሳሳይ አቶ በረከት ስምኦንና አቶ አዲሱ ለገሠ በብአዴን መካከለኛና ዝቅተኛ አመራሮች ላይ ያላቸውን የተመናመነ ተስፋ የተናገሩበት ምሬት የተቀላቀለበት ሚስጥራዊ ንግግር እንድንሰማው ያደረጉት ብአዴኖች ናቸው:: ከዚህ የምንረዳው የአማራውን የበረታ ኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት ወደ ጎሳ ብሔረተኝነት ድንክነት የመከርከም ታላቅ ተልዕኮ ያነገበው ብአዴን ክርከማው የታሰበውን ያህል እንዳልሰመረለት ነው::


## “በአውሮፓ አይሁድ በተገኘበት . . .

ተሳክቷል:: ሁለተኛም አብዮት ነበር:: የሙስሊም ወንድማማቾችን ሃይማኖታዊ ፋሽዝምን ነው ያስወገድነው:: ግብጽ ከእንግዲህ ወደ ኂላ አትመለስም:: ሁልጊዜም አብዮት ሲኖር ወደ ኂላ መመለስ የለም:: ምርጫውን አይተኸው ከሆነ እስላማዊ አክራሪዎቹ ምንም ድምጽ አላገኙም:: ፓርላማው የግብጽን ዜጎች የሚወክልና ትክክለኛ ዜጎችን የያዘ ፓርላማ ነው ብዬ አምናለሁ - ምንም እንኳን የመራጩ ቁጥር ብዙ ባይሆንም:: ያም የሆነበት ምክንያት ባለፉት ሁለት ዓመታት 8 ጊዜ ምርጫ በመካሄዳችን በመራጩ ሕዝብ ዘንድ መሰላቸት በመኖሩ ነው::

እንደሚታወቀው በመጀመሪያው የፈረንሳይ አብዮትና በመጀመሪያው ሕዝባዊ መንግሥት ምሥረታ መካከል ብዙ ችግሮች ነበሩ:: በማግና ካርታና በብሪታንያ ዴሞክራሲ መካከል የ400 ልዩነት አለ ፤ ዴሞክራሲ በዚያች አገር ለማደግ ብዙ ዓመታት ፈጅቶበታል:: እኛ ለአገራችን 200 ዓመት አንጠይቅም:: ሁሉንም ነገር ልናልፍበት የምንችለው ዴሞክራሲ ብቻ እንደሆነ እናምናለን:: ግብጽ በአህጉሩ ዴሞክራሲ የሌለባት አገር አይደለችም:: ከማንም በፊት ዴሞክራቲክ የነበረች አገር ነች:: እ.ኤ.አ. በ1923 ግብጽ ሕገ መንግሥት አርቅቃለች:: በዚያን ጊዜ አይሁዳዊ ሚኒስትሮች፣ የኮፕት ጠቅላይ ሚኒስትርና ሚኒስትር ነበረን:: እኛ በዚህ ዓይነት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ሳለን በአውሮፓ ጭፍጨፋና እልቂት እንደነበር ላስታውስህ ነው ይህን ያነሳሁልህ:: ያኔ በአውሮፓ አይሁድ በተገኘበት ይገደል ነበር፤ በኛ አገር ግን ሚኒስትር ሆኖ ይሾም ነበር:: ከማንም ትምህርት መውሰድ አያስፈልገንም:: እኛ የራሳችን መስመር ተከትለን ነው የምንሄደው::

**ግብጽ ከኢትዮጵያና ከኤርትራ ጋር ግንኙነት አላት:: እንደሚያውቁት በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ብዙ የሁለቱ አገሮች ዜጎች ከሞቱም በኋላ እስካሁን ሰላም ማምጣት አልተቻለም:: በዚህ ዙሪያ የግብጽ ሚና ምን ሊሆን ይችላል?**

እንድናሸማግላቸው ቢጠይቁን ያለምንም ጥርጥር እናደርገዋለን:: ግብጽ ቀጠናው የተረጋጋና ሰላም የሰፈነበት እንዲሆን ትፈልጋለች:: ምክንያቱም በቀጠናው ሕገ ወጥነት ሲሰፍን የጦር የመሣሪያ፣ የአደንዛዥ ዕጽና የአልኮል ንግድ እንዲሁም ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ነው የሚያስፋፋው:: ይኼ ደግሞ ለማናችንም አይጠቅምም::



## የዜጎች ድምጽ

(በዚህ ዐምድ ኢትዮጵያውያን የማኅበራዊ ድረ ገጽ ተጠቃሚዎችን የሚያወያዩና የሚያከራክሩ አንኳር ጉዳዮች ተመርጠው ይቀርባሉ)

ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም

# ከመጠምጠም መማር ይቅደም

በፌስቡክ የምንሰባሰበው ለመወያየት፣ አንዱ ከሌላው እንዲማር፣ መረጃዎችን በነጻነት እንድንለዋወጥ፣ ይህንን ሁሉ በማድረግ ራሳችንን ለማሻሻል፣ የእኛ መሻሻል እየተራባና እየተባዛ የአገርና የሕዝብ መሻሻል እንዲሆን፣ ከተቻለንም ከአገራችንና ከሕዝባችን አልፈን የምንታይ የዓለም አካል እንድንሆን መስሎኝ ነበር፤ ሳየው በዚያ መንገድ ላይ ያለንና ፌስቡክን ለበጎ ዓላማ እየተጠቀምንበት ያለን አይመስለኝም፤ ስለዚህ ወይ መታረም፣ አለዚያም በፌስቡክ ጊዜ ማጥፋቱን መተው ምርጫ ሊሆንብን ነው።

ምናልባት 99.99% በእኔ ሰፈር ያሉ የፌስቡክ ተሳታፊዎች ወደፌስቡክ የሚገቡት ለመናገር ነው፤ መናገር የህልውናቸው ምስክር ወይም ማረጋገጫ አድርገው የሚወስዱት ጥቂት አይደሉም፤ ካልተናገሩ የሌሉ ይመስላቸዋል፤ ዋናው ነገር መናገር ይሆንና የሚናገሩት ነገር ወይም ጉዳይ ሌላው ቀድሞ ከተናገረው ጋር የሚያያዝ (የሚቃወመው ወይም የሚደግፈው) ሳይሆን ፈጽሞ ወደተለየ ጉዳይ ውስጥ ገብቶ አዲስ ርእስ መክፈት የተለመደ ነው፤ የአብዛኛው ፍላጎት ማስተማር ወይም ማሳወቅ ነው፤ ማስተማር ወይም ማሳወቅ ቀላል ነው፤ መናገር የሚችል ወይም ፊደሉን አውቆ መጻፍ የሚችል ማስተማር ይችላል።

የትምህርት ቤት ጓደኛዬ በጃንሆይ ዘመን ትልቅ ሚኒስትር ነበር፤ በደርግ ዘመን ለብዙ ዓመታት ታስሮ ሲወጣ ሥራ አልነበረውም፤ ችሎታውን ስለማውቅ በዩኒቨርሲቲ እንዲያስተምር አመቻቸሁለትና ማስተማር ጀመረ፤ ከጥቂት ወራት በኋላ ስንገናኝ ‹‹እኔ ማስተማር ቀላልና እረፍት የሞላበት ሥራ ይመስለኝ ነበር፤ ለካ አንቅልፍ የሚያሳጣ ነው! እዝናናለሁ ባልሁ ቁጥር አንድ ክፍል ሙሉ ተማሪዎች ተሰብስበው ዓይኖቻቸውን እያቁለጨለጩ ምን እንደማስተምራቸው ሲጠብቁ ይታዩኛል! እረፍት ይነሡኛል!›› አለኝ፤ ከአንድ ዓመት በኋላ ማስተማሩን ተወ፤ ኅሊና ላለው ሰው ማስተማር ቀልድ አይደለም፤ ያደክማል፤ ለማስተማር መማር ያስፈልጋል፤ ለማሳወቅ ማወቅ ያስፈልጋል፤ ከመማር ይልቅ ማስተማር፣ ለማወቅ ከመጣር ይልቅ ለማሳወቅ መጣር የሚቀልለው ሰው የዕውቀት ሰው አይደለም፤ ሌላ ሥራ ቢመርጥ ይሻለዋል።

ሳያውቁ ለማሳወቅ አደባባይ መውጣት ከችኮላ ወይም ከስንፍና፣ ከትዕቢት ወይም ከግዴለሽነት የሚመጣ ነገር ይመስለኛል፤ ውሎ አድሮ ይጎዳል እንጂ አይጠቅምም፤ በአደባባይ መናገር ወይም መጻፍ የመጨረሻው መጋለጥ ነው፤ በአደባባይ መናገርና መጻፍ በሕዝብ ፊት መጋለጥ መሆኑን ብዙ ሰዎች አያውቁም፤ በአንጻሩ ደግሞ ብዙ ሰዎች ይህንን መጋለጥ ፈርተውትና ሸሽተውት የሚርቁት አሉ፤ መጋለጥን ፈርተው ዓይኖቻቸውን ዘግተው፣ ጆሮዎቻቸውን ደፍነው፣ አፋቸውን ለምግብና ለመጠጥ በቀር የማይጠቀሙበት፣ ዝምታ ወርቅ ነው እያሉ ወርቅ የሚሸምቱበት ብዙ ናቸው፤ ከሕዝብ ጋር እየተጓዙ፣ በሕዝብ መሀል እየኖሩ የሕዝብ ጉዳይ (ፖሊቲካ) አይመለከተንም የሚሉ የማሰብ ችሎታቸውን ህልውና ይጠራጠሩ፤ የማሰብ ችሎታ ከሌለ የማወቅ አምሮት ወይም ምኞት የሚኖር አይመስለኝም፤ የማወቅ አምሮት በሌለበት የማሳወቅ አምሮት ጎልቶ ሲወጣና ሲደናበር ማየት በጣም የተለመደ እየሆነ ነው፤ ፌስቡክ የሚባለው መድረክ የመደናበሪያ መድረክ እየሆነ ነው።

> ሳያውቁ ለማሳወቅ አደባባይ መውጣት ከችኮላ ወይም ከስንፍና፣ ከትዕቢት ወይም ከግዴለሽነት የሚመጣ ነገር ይመስለኛል፤ ውሎ አድሮ ይጎዳል እንጂ አይጠቅምም

የማሰብ ችሎታው የሌላቸው ሰዎች ከሁለት አንዱን መንገድ በመምረጥ፣ ወይም በሁለቱም መንገዶች በመጠቀም ይሳተፋሉ፡- የማያውቁትን ለማሳወቅ በመሞከርና በዘለፋ! የማያውቁትን ለማሳወቅ መሞከርና ዘለፋ የባሕርይ ግንኙነት አላቸው፤ አሁን እዚያ ውስጥ አንገባም፤ በተለያዩ መስኮች፣ በተለያዩ ጉዳዮች፣ በተለያዩ የዕውቀት ጥበቦች በሚያሰራጩት ፍንጥቅጣቂ በአእምሮና በመንፈስ ለመበልጸግ በመጣር ፈንታ በአጉል ትዕቢትና ፉክክር፣ በማይጠቅም ዘለፋና ማስፈራራት የፌስቡክን መድረክ ማበላሸትና ማርከስ ወደኋላ ይጎትተናል እንጂ ወደፊት አያራምደንም።

መሠረታዊ የማሰብ መነሻችን ሳንገነዘብ የማሰብ ትርምስምስ ውስጥ እንገባና መውጣት ያቅተናል፤ ለምሳሌ በዕውቀትና በእውነት መሀከል ያለውን ልዩነት ሳንገነዘብ እምነትን ስንሞግት የራሳችንንም ሆነ የሌላውን ጊዜ እናጠፋለን፤ ዕውቀትን በሙግት ለማጣራት ሲመጡብን ደግሞ ቶሎ ወደእምነት እንዞራለን፤ አጉል መሽከርከር ውስጥ እንገባለን፤

እንዲያው በሆነ ባልሆነው፣ ባወቅነውም ሆነ ባላወቅነው የመጣልንን ሁሉ መዘርገፍ አዋቂ አያሰኝም፤ ጎበዝ አያሰኝም፤ ብልህ አያሰኝም፤ ግን ባለጌ ያሰኛል፤ ባለጌ ነጻነትን አያውቅም፤ ለባለጌ ስድነት ነጻነት ይመስለዋል፤ ነጻነት ባለቤቱ ያጠረው ገደብ ወይም ወሰን አለው።


# ኮከብ ብርሃን
## የባህል ሕክምና ማዕከል

ማንኛውም ባለጉዳይ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በትህትና በማስተናገድ ሳይ ሲሆኑ በአሁኑ ሰዓት ትክክለኛ ፈውስ የተገኘላቸው በሽታዎች በከፊል፡-

- ለሆድ ሕመም
- ለእጅና ለእግር ቁርጥማት
- ለአስም
- ለሾተላይ
- ለራስ ሕመም
- ለእግር ፈንገስ
- ለሚጥል በሽታ
- ለማዲያት
- እጁን ለሚጠባ
- ለትምህርት
- ለእጅ ሰብእ
- ለጭርት ወይም ማሳከክ
- ለአይነ ጥላ
- ለወር አበባ መብዛት
- ሌሊት ለሚሸና

በተለይ የብዙ ሰዎችን ችግር የሆነውን የስንፈተ ወሲብ /በመቀባት/ ብቻ ፈውስ ይሰጣል።

አድራሻ፡-

ሐና ማርያም ቀለበት መንገድ ንግድ ባንክ ፊት ለፊት

ለበለጠ መረጃ፡- 0911 808241 /0913 778746/ 0912 635069

በእውነት ስለ እውነት እንተጋለን!!


# ረኀቡና ኢሕአዴጋዊ...

ይፋ አደረገ። ይህንን እውነታ በማስረጃ ለማስደገፍ ያህል ‹‹የሰሞኑ የረኀብ ፖለቲካ›› በሚለው የፓርቲ ሰነድ ከገጽ 7-8 የሚከተለውን ይላል፡-

‹‹በአንዳንድ የደቡብ አካባቢዎች አደጋውን በወቅቱ ካለማየት ጋር ተያይዞ ባለፈው ዓመት 26 ያህል ሕጻናት ለሞት የተዳረጉበት ሁኔታ ተከስቷል። ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ በረኀብ ምክንያት የተፈናቀሉ ዜጎች የሉም። አልፎ አልፎ በአፈጻጸም ጉድለት ምክንያት እንደተጠቀሰው የሟች ዜጎች ቢኖሩም በአጠቃላይ በመቶ ሺዎች ቀርቶ በመቶዎች የማይሞቱበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በተወሰኑ አካባቢዎች የሚታየው የአፈጻጸም ጉድለት ካስተካከልን ምንም ዜጋ የማይሞትበት ሁኔታ መፍጠር እንደምንችልም ጥርጥር የለውም።››

እንዲህ እውነቱ ተቀናንሶና በብዕር ቆንጨራ ተከታትፎ ቢቀርብም በአደባባይ ያለው ሚስጥር ሃቁን መሸፋፈን አልቻለም። ዛሬም ዜጎች በረኀብ ሰቆቃ ውስጥ እየኖሩ ነው። ሕይወታቸው እየተቀጠፈ እየተመለከትን የ‹‹ምጥቁ መሪ›› ተከታዮች ረኀብ የለም ይሉናል። ችግር የተከሰተው ‹‹ምናምንቴ›› የሚል ስያሜ በተሰጠው አየር መዛባት ምክንያት ድርቅ ስለተከሰተ እንደሆነ ይሰብኩናል። ፍቱን መድሃኒቱም በተግባር የተረጋገጠው ‹‹ኪራይ የሚሰበስበው›› ስትራቴጂያቸው እንደሆነ ይነግሩናል። በርግጥ ሃቁን በትክክል ቢያስቀምጡ ከትናንትናው ምላሳቸው ጋር ስለሚጣሉ አጣሞ ማቅረብ ግዴታቸው ይሆናል። ምንም እንኳን ያሳምንልናል ብለው የሚያቀርቡት መከራከሪያ ከተጨባጭ ሃቁና መሬት ላይ ካላው እውነታ የትየለሌ በመሆኑ በሕዝቡ ትዝብት ላይ ቢወድቁም!

እዚህ ላይ ማንም አእምሮ ያለውና የዓለምን ሁኔታ የሚከታተል ሰው የአየር መዛባት፣ የዝናብ እጥረት አልተከሰተም አይልም። ከአገዛዙ ከበለጠ የድርቅ ባሕሪያና ትርጉም መረዳት የሚያቅተውም አይደለም። በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም የምግብ ምርት ወይም የውኃ አቅርቦት በመቀነሱ ከፍተኛ ጫና የሚያስከትሉ የእርጥበት እጥረት መከሰቱን የሚክድ የለም። የድርቅ መነሻ ምክንያቱ ከመደበኛና ከሚጠበቀው በታች በአየር ጠባይ መለያየት የተነሳ የዝናብ እጥረት መሆኑ የሚዘነጋ አይደለም። በዓለም አቀፍ ደረጃም በአየር ጠባይ ለውጥ ምክንያት በተለያዩ ዘመናት አገሮች በድርቅ ሲጠቁ ተመልክተናል።

ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ ባለፈው ክረምት ጓድ ኃይለማሪያም ደሳለኝ ከውጭ የመጡ የአገሬ ሰዎች በሚሊኒየም አዳራሽ ሰብስቦ ያሰማው ‹‹ኢሕአዴጋዊ እውነታ›› የኢትዮጵያውያን መነጋገሪያ ሆኖ ነበር። በተለይ በካሊፎርኒያ የአሜሪካ ዜጋ በድርቅ እየተሰቃየ መሆኑ አስረግጦ ሲናገር የተሰማው ጭብጨባ እስከዛሬም ጆሮዬን ይሰቀጥጠኛል። የሆነው ሆኖ ‹‹ካሊፎርኒያ በድርቅ ተሰቃየች›› የሚለው አባባል የትኛውን ግብ ለማሳካት በጭብጨባ እንደታጀበ የሚያውቁት አጨብጫቢዎች ብቻ ቢሆንም የገባንበትን የሰብዕና መላሸቅ አጉልቶ የሚያሳይ ነበር። የአውስትራሊያ ወይም የካሊፎርኒያ ሕዝብ በድርቅ ቢጠቃ ደስ ይለናል ማለት ነው?

የአገጣሚ ነገር ሆኖ የዛሬ ሳምንት እኔና ተወልደ በየነ (ተቦርነ) ለኢሳት የገቢ ማስገኛ ዝግጅት የካሊፎርኒያ እምብርት ወደሆነችው ሎስ አንጀለስ (ተቦርነ ‹‹ላይ አርማጭሆ›› ይላታል) ሄደን ነበር። የፕሮግራሙ አዘጋጅ ኮሚቴ የእንኳን ደህና መጣችሁ የመክፈቻ ንግግር ሲያደርጉ ‹‹እንኳን በድርቅ ምክንያት እየተሰቃየች ያለችውን ካሊፎርኒያ በሰላም መጣችሁ!›› በሚል ነበር የጀመሩት።ነይህንን የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር በአርምሞ ሲያዳምጡ የነበሩት ተሰብሳቢዎች በጭብጨባ አስከትሎም የማያባራ ሳቅ አጀቡት። መቼስ! ተንኮል ካልሆነ በስተቀር ጭብጨባና ሳቅ ምን አመጣው? እንኳንም ጓድ! ኃይለማርያም በስብሰባው አልኖረ! እንኳንም በሚሊኒየም አዳራሽ የተገኙ የካሊፎርኒያ ነዋሪዎች አልሆኑ።

እናማ የስብሰባው አዘጋጆች ፕሮግራም ከተጠናቀቀ በኋላ በያዙልን ዕለታዊ መርሐ-ግብር መሠረት ካሊፎርኒያን ያስጎበኙ ነበር። የድሮ ካድሬ ነገር ሆኖብኝ የምንሄድበት መኪና በቆመ ቁጥር ነጩን፣ ጥቁሩን፣ ስፓኒሹን፣ አፍሪካዊውን ካሊፎርኒያ ‹‹ድርቁ እንዴት ነው? ምን ጉዳት አስከተለ?›› የሚል ጥያቄ አነሳ ነበር። ያለማጋነን ጥያቄ ከመለሱልኝ ሰዎች ውስጥ ዘጠና በመቶው ድርቅ መኖሩን አያውቁም። የተቀሩት ውኃ ለመቆጠብ የሻወር ቤታቸውን የውኃ ወንፊት እንዳጠበቡ ነግረውናል። ከፊሎቹ ለውኃ ቁጠባ ሲባል መኪናቸውን በሁለት ሳምንት አንዴ እያጠቡ መሆኑን እያዘኑ አጫውተውናል። ሐዘናቸውንም ተጋርተነዋል። የሻወር ቤት ወንፊት ከማጥበብ፣ መኪናን በሳምንት ▶

## ልዩ ዘገባ



ሙሉቀን ተስፋው

# ሰሚ ያጣው የሰመጉ ጩኸት

• ‹‹ብልታችንና የሴቶቻችን ጡት በፒንሳ እየተጠመዘዘ በወረዳው ፖሊስ ጣቢያ ከተሰቃየን በኋላ ተባረናል›› ከምዕራብ ሸዋ የመጡ የአማራ ተወላጆች

ሰብአዊ መብት ጉባኤ ጽሕፈት ቤት ስደርስ ቤቱ በጋዜጠኞችና በውጭ ዲፕሎማቲክ ቡድን ተወካዮች ተሞልቶ ነበር፡፡ ሰመጉ ‹‹ብሔር ተኮር ማፈናቀልና እንግልት እንዲሁም በልማት ስም በዜጎች ላይ የሚፈጸም የማፈናቀልና የንብረት ማውደም በአስቸኳይ ይቁም!›› በሚል ያዘጋጀውን መግለጫ ለመስማት ነበር፡፡ ከአፋር ክልል መንግሥት የቴምር ዛፍ የወደመባቸውንና በምዕራብ ሸዋ ዞን ኖኖ ወረዳ ሀብት ንብረታቸው ተቃጥሎ የተባረሩ አማራ አርሶ አደር ተወካዮችን ጭምር በማስመጣት ምስክርነት እንዲሰጡ ፊት አካባቢ ተቀምጠዋል፡፡ የተለያዩ የሰመጉ የሥራ ኃላፊዎች መግለጫውን ካነበቡ በኋላ ከሁለቱም ቦታ የመጡ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች የነበረውን ሁኔታ ሲናገሩ የሚያሳዝንም ተስፋ የሚያስቆርጥም ነበር፡፡

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን ኖኖ ወረዳ በተለያዩ ቀበሌዎች ውስጥ በእርሻ ሥራ የሚተዳደሩ የአማራ ተወላጆች የተለያየ ዓይነት ሰብሎችን በመዝራት ራሳቸውን፣ ቤተሰባቸውንና ክልሉን በአጠቃላይ ለአገሪቱ ገበያ የሚቀርብ ምርት በማምረት የሚታወቁ ውጤታማ አርሶ አደሮች ነበሩ፡፡ ይሁንና በአካባቢው የሚገኙ ባለሥልጣናትና የጸጥታ ኃፊዎች እነዚህን አርሶ አደሮች ‹‹እናንተ የዚህ አካባቢ ተወላጅ ሳትሆኑ ሀብት እያፈራችሁ የአካባቢው ተወላጅ ግን ከእናንተ ያነሰ ገቢ ያላቸው ናቸው፤ ይህን ገቢ ያገኛችሁት በእኛ መሬት ላይ ነው፤ ስለዚህ የክልሉ ተወላጆች ባለመሆናችሁ ክልሉን ለቃችሁ ውጡ›› በማለት ንብረታቸውን በተለያየ ጊዜ በመንጠቅ እነዚህን አርሶ አደሮች በተለያየ ጊዜ ለእስራት ዳገዋቸዋል፡፡ የአካባቢውን ሕዝብም ‹‹በእናንተ መሬት ነው ሀብት ያፈሩት›› እያሉ ጥላቻና ግጭትን ሲሰብኩ እንደቆዩ በሰመጉ በ136ኛ መግለጫና ምስክርነታቸውን በሰጡ አርሶ አደሮች ተነግሯል፡፡

ምስክርነታቸውን ከሰጡት መካከል በአካባቢው ተወልዶ ያደገው አቶ አለሙ አስፋው ‹‹በ1996 ዓ.ም. በዞኑ መዳሉ ወረዳ 52 እንዲሁም በ2002 ዓ.ም. ደግሞ በዳኖ ወረዳ 152 የአማራ ቤትና ንብረት ሲቃጠል ምንም የተወሰደ እርምጃ የለም›› ሲል ከዚህ በፊትም ስለነበረው ብሔር ተኮር ጥፋት ይናገራል፡፡ የሰመጉ መግለጫና ገበሬዎቹ እንደሚያረጋግጡት መጋቢት 27 ቀን 2007 ዓ.ም. አቶ ዘውዱ እንዳለ የተባለ የኦሮሞ ተወላጅ ተገድሎ ይገኛል፡፡ ተገድሎ የተገኘውን ገዳይ ሁሉም ኅብረተሰብ ወንጀለኛውን ለማገኘት እየተረባረበ ባለበት ሰዓት ‹‹ይህ ግድያ የተፈጸመው በአማራ ብሔር ተወላጆች ነው›› በማለት የኖኖ ወረዳ የፖሊስ አዛዥ ኢንስፔክተር ኃይሉ ድሪባ፣ የኖኖ አሎ ቀበሌ ሊቀመንበር አቶ ጎሳየ ገችና መቶ አለቃ ገነነ በየነ የተባሉ የፖሊስ አባላት የቀበሌና የፖሊስ አባላትም በማስተባበር የአካባቢው ሕዝብ በአካባቢው በሚኖሩ የአማራ ተወላጆች ላይ እንዲነሳሳ በማድረግ ሚያዚያ 9 ቀን 2007 ዓ.ም. 85 አርሶ አደር አባውራዎችን ለእስራት ከዳረጓቸው በኋላ ቅዳሜ ማለትም ሚዚያ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. ከጠዋቱ በ3፡00 ሰዓት አካባቢ ዘር በመምረጥ የአማራ መኖሪያ ቤትና ንብረት ነው ያሉትን እየመረጡ በእሳት እንዲቃጠል አድርገዋል፡፡



በእሳት የተቃጠለ የአርሶ አደር መኖሪያ ቤት በኖኖ ወረዳ ሚያዚያ 2007

የታሰሩትን ወንዶችና ሴቶችም ብልታቸውንና ጡታቸውን በፒንሳ እየጠመዘዙ ቤቱን ለሚቃጠልበት የሚውል ለነዳጅ በማለት ከእያንዳንዳቸው 300 ብር ተቀብለዋቸዋል፡፡ ከ27 ገበሬዎች ብቻ 8100 ሰብስበዋል፡፡ ገበሬዎቹ ሲወጡ ሀብት ንብረታቸውም ሆነ የነበራቸው ነገር ሁሉ ወድሞ ነው ያገኙት፡፡ በንግድ ሥራ የምትተዳደር ወ/ሮ ጽጌ የተባለች የአካባቢው ነዋሪ የነበረውን ሁኔታ ስትገልጽ ‹‹ቤታቸው ሲቃጠል ልብሳቸውን ሁሉ አጥተው ራቁታቸውን ደብቂን እያሉ ወደኔ በርካታ ልጆች መጡ፡፡ ማጀት አስገብቼ ወደ ፖሊስ አዛዡ ቢሮ በመሄድ ‹ኧረ ተው በሰው ስቃይ እንዲህ አትደሰት?› ስለው ገና አንቺም ትቃጠያለሽ አለኝ›› በማለት የነበረውን ሁኔታ ትናገራለች፡፡

አቶ ዓለሙ አስፋው በበኩላቸው ‹‹የሚሊሻ ኮማንደር ነኝ፡፡ በጊዜው ሰላሳ ጎራሽ ክላሽ ይገኔ ነበር፡፡ የፖሊስ አዛዡ አቶ ደመና ግዘውን ሲገድላቸው ቆሜ እየተመለከትኩ ‹እንዴ ተው ሕግ ባለበት አገር› ስለው ‹አማራ እኮ ነው አይመለከትህም› አለኝ፤ በያዝኩት ጠመንጃ አይደለም እርሱን 30 ሰውም መግደል እችል ነበር፤ ግን ያን ባደርግ የሁሉም ችግር መንስኤው እርሱ ነው ስለምባል እያነባሁ ዝም አልኩ፤ እኔ ሰላም ለማስከበር ላይቤሪያ ድረስ ሄጃለሁ፤ ሆኖም በአገሬ ሰላም የለም፡፡ የሰው አገር ሰላም ሳስከብር በአገሬ ላይ ግን ስለሰላም መናገር እንኳን አልቻልኩም›› ሲል በምሬት ገልጿል፡፡

አቶ ደመና በሚያዚያ 12 ቀን 2007 ዓ.ም. ልጃቸውን ሊድሩ ዘመድ አዝማድ ሁሉ ተጠርቶ ዝግጅቱ ሁሉ አልቆ ነበር፡፡ ሆኖም የልጃቸውን ደስታም ሳይመለከቱ ሰርጉ አንድ ቀን ሲቀረው በመንግሥት የፖሊስ አዛዥ ተቀጥቅጠው ሞተዋል፡፡ የሚች ወንድም ‹‹ወሊሶ ሆስፒታል ሳይደርስ ነው የሞተው፤ የግፋቸው ግፍ ራሳቸው የገደሉትን አስከሬን ለምርመራ አዲስ አበባ መላክ አለብን

> ነሐሴ ወር መጨረሻ ላይ ሮንድ እንዲጠብቅ የተመደበውን አቶ አቢ ተክለማርያም በጥይት ተደብድቦ ተገድሏል። ገበሬዎቹ እንደሚናገሩት ከሚለብሱት ልብስ ጀምሮ በጉራጌ ዞን አበሽጌ ወረዳ ያስጠጓቸው የአካባቢው ሰዎች እንደሰጧቸውና ተመልሰው ግን ለመኖር እስካሁን አዳጋች እንደሆነባቸው ነው ለዝግጅት ክፍላችን የገለጹት

ብለው 6000 (ስድስት ሽህ ብር) አምጣ አሉኝ፡፡ የለኝም ስላቸው አስከሬኑን አውላላ ሜዳ ላይ አስቀምጠው መውሰድ እንደማልችል ተነገረኝ፡፡ አስከሬኑ ሜዳ ላይ ፈራርሶ ከሚቀር በማለት ተበዳድሬ ሰጠው፡፡ የራሴን እንኳ እንዳልሰጥ ያለኝን በሙሉ አቃጥለውታል፡፡ የግፍ ግፍ ነው የተሰራብን›› በማለት በእንባ ነው የተናገሩት፡፡

ሰመጉ በ136ኛ መግለጫው የአንድ ሰው ማለፉን፣ 10 ሰዎች ላይ ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት መድረሱን፣ 99 የእሳር ክዳን ቤቶች በእሳት መቃጠላቸውንና 25 የቆርቆሮ ክዳን የመኖሪያ ቤቶች በእሳት መውደማቸውን ገልጿል፡፡ የአርሶ አደሮቹን መኖሪያ ቤትና ንብረት ቃጠሎ ተከትሎ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሴቶች፣ ሕጻናትና አቅመ ደካሞች የሚገኙባቸው ተፈናቃዮች በአካባቢው በመሰደድ ወደ ደቡብ ክልል ጉራጌ ዞን አበሽጌ ወረዳ ድንኳን ውስጥ ተጠልለው ሲረዱ መቆየታቸውንም አስታውሷል፡፡

ሰመጉ በጋዜጣዊ መግለጫው ጥፋት የፈጸሙት የመንግሥት አካላት ምንም አይነት ሕጋዊ እርምጃ እስካሁን እንዳልተወሰደባቸውና የተፈናቀሉ ገበሬዎችም ተመልሰው በሰላም መኖር አለመቻላቸውን ጠቅሷል፡፡ ይባስ ብሎም ነሐሴ ወር መጨረሻ ላይ ሮንድ እንዲጠብቅ የተመደበውን አቶ አቢ ተክለማርያም በጥይት ተደብድቦ ተገድሏል፡፡ ገበሬዎቹ እንደሚናገሩት ከሚለብሱት ልብስ ጀምሮ በጉራጌ ዞን አበሽጌ ወረዳ ያስጠጓቸው የአካባቢው ሰዎች እንደሰጧቸውና ተመልሰው ግን ለመኖር እስካሁን አዳጋች እንደሆነባቸው ነው ለዝግጅት ክፍላችን የገለጹት፡፡ በአዲሱ ዓመት ዋዜማ በጥይት ተደብድቦ የተገደለውን አቶ አቢን ተክለማርያምን አገዳደል በተመለከተ ሲናገሩ ‹‹የሌሊት ጥበቃ ሮንድ ከአራት ኦሮሞዎች ጋር ተመደበ፡፡ ሆኖ ተብሎ እንደዚህ እንደተመደበ የሚያውቀው ነገር አልነበረም፡፡ ነገር ግን በጥይት ተደብድቦ ተገደለ›› በማለት የተሰራውን ሴራ ይገልጻሉ፡፡ እንደአርሶ አደሮች ገለጻ ከሆነ ይህን በዋናነት ሲያስተባብሩ የነበሩ የኦሕዴድ/ኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ምንም ዓይነት ሕጋዊ እርምጃ አልተወሰደባቸውም፡፡ አርሶ አደሮቹም የወደመባቸው ንብረት ሊሰጣቸው ቀርቶ ተመልሰው እንኳን ሕጋዊ መሬታቸውን ለማልማት እንዳልቻሉ ነው የሚገልጹት፡፡

በተያያዘም በአፋር ክልል በአሳይታ ወረዳ ዋሙሌ ቀበሌ በስኳር ኮርፖሬሽን ለሸንኮራ አገዳ ልማት በሚል የቴምር ዛፍ የወደመባቸው ከፊል አርብቶ አደሮችን ሕይወት አመሰቃቅሏል፡፡ የተንዳሆ ስኳር ፕሮጀክት የነዋሪዎቹን ፈቃደኛነት ሳይጠይቅ ካሳም ሳይፈጽም ከ8300 በላይ የቴምር ዛፎች እንደተመጠሩና ነዋዎቹም ችግር ላይ መሆናቸውን ሰመጉ በ138 ልዩ መግለጫው ይፋ ማድረጉ የሚታወስ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ችግሩ አለመቆሙን ነው በጋዜጣዊ መግለጫው ይፋ የተደረገው፡፡ ከአፋር ክልል የመጡት ነዋሪዎች እንደሚሉት ‹‹አካባቢውን ለቀን ወደ ጅቡቲና ሶማሊላንድ እንድንሰደድ ይፈለጋል፡፡ እኛ ግን የምንሄድበት የለንም፡፡ የምንመገበው ቴምር ነው፤ ለቤት መሥሪያና ለመኝታም የምንጠቀመው የቴምር ዛፍን ነው፤ ሆኖም አሁን ሁሉም እንዳልነበር ሆኗል›› ሲሉ ገልጸዋል፡፡ ሰመጉ በ138 ልዩ መግለጫ የአፋር ባህልን መሠረት በማድረግ አንድ የቴምር ዛፍ ሲቆረጥ ካሳ የሚሰጠው ሰባት የቁም ከብት እንደሆነ ጠቅሷል፡፡ ሆኖም ነዋሪዎቹ እስካሁንም ምንም ዓይነት ክፍያ ካለማግኘታውም ባሻገር አቤቱታቸውንም የሚሰማቸው አካል ማጣታቸውን ጭምር በምሬት ገልጸዋል፡፡

(ይህ ጽሑፍ የተዘጋጀው ሰመጉ ሕዳር 16 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠውን ጋዜጣዊ መግለጫ እንዲሁም 136ኛና 138 ልዩ መግለጫዎቹን መሠረት በማድረግ ነው)

---

ሁለት ጊዜ ከማጠብ በላይ ምን ስቃይ አለ? አትክልትን ከሳምንት አምስት ቀን ሁለት ቀን ውኃ እንዲጠጡ ከማድረግ በላይ ምን የሚያበሳጭ ነገር አለ?

የአጋጣሚ ነገር ሆኖ በግዛቱ የመንግሥት ተቋም ውስጥ የሚሠራ ሙያተኛ ከአስጎብኚዎች አንዱ ነበር፡፡ ግለሰቡ ካሊፎርኒያ ያጋጠማት ችግር ጓድ ኃይለማሪያም ከጠቀሱት በተቃራኒ፣ ከልክ በላይ መብላት የሚመጣ ውፍረት (Obesity) መሆኑን ነገረን፡፡ ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ እንዲሉ ወዳጃችን የካሊፎርኒያ ችግር ከመጠን በላይ ምግብ በመብላትና የአካል እንቅስቃሴ ባለማድረግ የሚመጣ የሰውነት ውፍረት እንደሆነ አጫወተን፡፡ በመፍትሔ ደረጃም በግዛቱ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ‹‹Child obesity school program›› ቀርጸው ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆኑን ነገረን፡፡ በየመቶ ሜትሩ የምናያቸው የተዘረጠጡ ሕጻናት ለፕሮግራሙ ተገቢነት የሚያረጋግጡ ነበር፡፡ እርግጥም ካሊፎርኒያን ጨምሮ በመላው አሜሪካ ጭንቀትና ስቃዩ የዜጎች የስብ ክምችት መሆኑን ለማወቅ ብዙ መልፋት አይጠበቅም፡፡ ለጥቂት ደቂቃዎች ወደኢንተርኔት ጎራ ያለ ሰው ከአሜሪካ አጠቃላይ ሕዝብ 78 ሚሊዮኑ (ከዚሁም 12 ሚሊዮን ሕጻናት) በውፍረት ግዝፈት መጠቃቱን ይመለከታል፡፡ ዘለግ አድርጎ ለተመለከተ ደግሞ የሰውነት ግዝፈት መጠን (obesity rate) በውፍረት በሽታ የግዛቶቹ ተደርድሮ ያያል፡፡ ለምሳሌ ካሊፎርኒያ 24.1%፣ ሚሲሲፒ 35%፣ ቨርጂኒያ 35.1% ወዘተ. እያለ ይቀጥላል፡፡

እነዚህን የመሳሰሉ አገሮች በአየር መዛባት ምክንያት ድርቅ ሲከሰትባቸው ትክክለኛ ፖሊሲ በመቅረጽ ዜጎቻቸውን ታድገዋል፡፡ የረጅምና የአጭር ጊዜ ስትራቴጂያዊ ዕቅዶችን ከማውጣት ባሻገር ተስማሚ ቴክኖሎጂ በመምረጥ፣ የውኃና አፈር አጠባበቅ ተግባርን በማሻሻል፣ የግብርና ምርት ውጤቶችን ወደውጭ እንዳይወጡ በማገድ፣ የገጠርና የከተማው ልማት በማቀናጀት ወዘተ. ዘላቂ መፍትሔ አስቀምጠዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሰፋፊ ዘመናዊ እርሻዎች በማስፋፋት፣ የግብርና ምርታቸውን በከፍተኛ እጥፍ በማሳደግና፣ የሕዝቡን የመግዛት አቅም በማጎልበት በድርቅ ምክንያት የሚከሰተውን አደጋ ከቁጥጥራቸው ውጪ እንዳይሆን አድርገዋል፡፡ ድርቅ ተፈጥሯዊ ነውና በማንኛውም ሰዓት ይመጣል፤ ግን ደግሞ እዚህ ግባ የማይባል ጉዳት አያደርስም፡፡ በፖለቲካው መስክም ቢሆን የገነቡት ዴሞክራሲያው ሥርዓት ሁለንተናዊ ልማት ለማረጋገት የበኩሉን ድርሻ ተወጥቷል፡፡ ያለነጻነት ሁሉን አቀፍ ልማት ማምጣት እንደማይቻል ተገንዝበው ለዜጎቻቸው ነጻነት አጎናጽፈዋል፡፡

እንግዲህ በዓለም ያለው እውነታ ይህ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ‹‹የሞኝ ለቅሶ መልሶ መላልሶ›› እንዲሉ ገዢዎቻችን በስልጣን ላይ ከወጡ ጀምሮ በየሁለት ዓመቱ የሚከሰተውን ከድርቅ የተሻገረ ረኀብ በአየር ጠባይ ለውጥ ምክንያት እንደሆነ ሊያስረዱን ይሞክራሉ፡፡ አገዛዙ ሥልጣን በያዘ ሁለት ዓመታት ጀምሮ መጀመሪያ 6 ሚሊዮን፣ ቀጥሎ 10 ሚሊዮን፣ በማስከተል 14 ሚሊዮን ሕዝብ በረኀብ ተጋልጦ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ 15 ሚሊዮን ኢትዮጵያዊ የረኀብ አደጋ አንዣቦበታል፡፡ እነዚህ ጥሬ ሃቆች የሚካዱ አይደሉም፡፡ በኢትዮጵያ ቀይ፣ ጥቁር፣ መረሬ አፈር ላይ የተነጠፉ እውነታዎች ናቸው፡፡ ዛሬም አገዛዙ በሚከተለው ፖሊሲ ምክንያት ራሳችንን መመገብ አቅቶን አቁማዳችንን ለመጽዋት ክፍት አድርገናል፡፡ አገዛዙ ዴሞክራሲያዊ፣ ሰብአዊና ሌሎች የሕዝብ መብቶችን የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን እስካልቀየረ ወይም ሥርዓቱ እስካልተቀየረ ድረስ የወደፊት ዕድላችን የከፋ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ሆኗል፡፡ የፊተኛው መፍትሔ እያለፈበት ይመስላል፡፡ የሥርዓት ለውጥ የሚለው ደግሞ ይበልጥ ተቀባይነት ማግኘቱ የሚታይበት ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ፍጥነቱ በደረሰው መከራና አበሳ፣ በደረብን ቁጭት ልክ ባይሆንም፡፡ ዞሮ ዞሮ አገራችን የገባችበትን የረኀብ አዙሪት ትግሉን ከሚያዘውሩት ቁልፍ ጉዳዮች አንዱ መሆኑ አልቀረም፡፡

# እድገቱ ለማን ነው . . .

የሚያንጸባርቁ መሆናቸው ነው። በእኔ ግምት አንዳንድ ባለሥልጣናት እንዳሉት፣ ያቀረቡት የችግሩን ጫፍ እንጂ ሁሉንም አይደለም። ፈረንጆች እንደሚሉት ‹‹This is the tip of the iceberg›› በምንም ዓይነት መስፈርት ባየው ይኼን የመሰለ ያልታሰበ ምርምርና ጥናት ለሕዝብ ይፋ ማድረግ የሚመሰገን እንጂ ለድለላና ለሺንገላ ነው የሚል ግምት የለኝም። እርግጥ ነው፣ የውጭ ተቋሞች ለምሳሌ ዓለም ባንክ፣ የተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት፣ ግሎባል ፋይናንሺያል ኢንተግሪቲ፣ ዩኒቨርስቲ ኦፍ ማሳቹሴትስና ሌሎች በኪራይ ሰብሳቢነት፣ ጉቦ፣ አድልዎ፣ ሙስናና ከአገር በገፍ የሚሸሽ ግዙፍ ሀብት ጥናቶች አድርገው ለውጥ አልታየም። ሁኔታው እየተባባሰ ሄዶ የሕዝብ ምሬት ወደ አደገኛ ደረጃ ተለውጧል። ስለዚህ ተመልካቾች ጥናቱ ‹‹የሺንገላና የሕዝብ ማባበያ ነው›› ቢሉ አይፈረድባቸውም። ሆኖም፣ ሁሉን ነገር እየተጠራጠርንና እየተቸን ዕድሎችና የለውጥ ክፍተቶች እንዲያመልጡን ማድረግ በታሪክ ያስጠይቀናል። ከዚህ በፊት ተከታታይ የዴሞክራሳዊ አገዛዝ ሥርዓት ለውጥ ዕድሎች ያመለጡን በምን ምክንያት ነው? የሚለውን ጥያቄ ማስተናገድ አለብን እላለሁ። በአጭሩ ሐሳባችን ለመለወጥ ፈቃደኛ ስላልሆንና ተባብረን ለመሥራት ስላልቆረጥን ነው።

## ምስጋና

በመጀመሪያ ጥናቱን ላካሄዱት ባለሞያዎች አድናቆቴንና አክብሮቴን አገልጻለሁ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የጀመሩት ውይይት እየሰፋ ሄዶ፣ ሰፊውን ሕዝብና የተቃዋሚውን ክፍል አሳትፎ ወደ ዋናው መሠረታዊ ወይንም ሥርዓት ወለድ የአገዛዝ ሁኔታ እንደሚሸጋገር ያለኝን ተስፋና ምኞት እገልጻለሁ። ይኼን የምልበት ምክንያት፣ የችግሩ መጠን፣ ጥልቀትና ስፋት በጥገና ሊለወጥ የማይችል መሆኑን ስለተረዳሁና የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ስለማምን ነው። ይኼን በሚመለከት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተናገሩት የችግሩን ጥልቀት ያሳያል። ‹‹ችግሩን የፈጠርነው እኛው ነን፣ እራሳችን ልዩ ልዩ የጥቅም ሰንሰለቶች ስላሉን፣ እነሱ እንዳይፈርሱብን ወይንም እንዳይነኩ አሁን በስብሰባ ላይ የተነጋገርነውንና የተስማማንበትን ጉዳይ ከስብሰባው ስንወጣ በተግባር እንዳይገለጽ እናደርጋለን።›› በስብሰባው ከተገኙት የፓርቲና የመንግሥት ባለሥልጣናት መካከል በኪራይ ሰብሳቢነት፣ በጉቦ፣ በጎሳዊ አድልዎ፣ በሙስና በሥልጣን ብልግና የተበከሉ ግለሰቦች እንደነበሩ ይነገራል። እነዚህ ግለሰቦች ድርጅቶቻቸውን ሽፋን አድርገው ማንኛውም ሕዝብን የሚጠቅም ለውጥ እንዳይመጣ እንደሚያርጉ እገምታለሁ። ይኼ ከሆነ ከገዢው ፓርቲና ከመንግሥት ተወካዮች ውጭ አግባብ ያላቸውን ተቋሞችና ግለሰቦች ያላሳተፈው ጥናት አበዳሪዎችን፣ የውጭ መንግሥታትንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመሸንገል የተደረገ ጥናት ነው የሚለውን ትችት ያጠናክረዋል።

ያም ሆነ ይህ፣ ጥናቱ እንዳሳየው በጸረ ሙስናና ሌላ የሕግ አስፈጻሚነት ሥራ የተሰማሩት ሠራተኞች የሚከላከሉትና ለፍርድ የሚያቀርቡት ዝቅተኛውን ‹‹ወንጀለኛ ወይም ኪራይ ሰብሳቢ›› ነው። ዋናዎቹ ከፍተኛ ኪራይ ሰብሳቢዎች በራሳቸው ላይ ትችት አቅርበው በራሳቸው ላይ ክስ ለማቅረብ የሚችሉ አይመስለኝም። መንግሥትና ገዢው ፓርቲ ከቁንጮው የተሰገሰጉትን ከፍተኛ ባለሥልጣናትና ኪራይ ሰብሳቢዎች አይነካቸውም። አንድ ታዛቢ እንዳስቀመጠው ‹‹መንግሥትና ገዢው ፓርቲ የከፍተኛ ኪራይ ሰብሳቢዎችና ጉበኞች መከታ፣ ምሺፍና ሺፋን ሆኗል።›› ውይይቱ መልካም ነው፣ ከውይይቱ በኋላስ እያንዳንዱ ባለሥልጣን ወደ ፈጠረው ‹‹የጥቅም ሰንሰለት›› ይዞራል ወይንስ አይዞርም? የሚለው ጥያቄ በድርጊት ይታያል።

አስኳል የአስተዳደር ችግሮችን ስገመግም ደላላዎች በቀን ብዙ ሚሊዮን ብር ካፒታል ያሽከረክራሉ፣ የአየር በአየር ንግድ ተስፋፍቷል፣ ከቀረጥ ነጻ የሆነ ንግድ ይካሄዳል፣ የጥቁር ገበያና በአጭር ጊዜ ሳይሠሩ መክበር ተቋማዊ ሆኗል። መንግሥት የሚገባውን ቀረጥና ሌላ የአገር ውስጥ ገቢ ለመሰስብ አልቻለም። የፍርድ ሥርዓት የሚተዳደረው በጉቦ ነው። አገልግሎት የሚሰጠው በጉቦና በወገን መረብ ነው›› ወዘተ. ሲባል መንግሥት የለም ወይስ አለ ወደሚል ጥያቄ ያመራኛል። እንደ ኢትዮጵያ ባለ አንድ ፓርቲ በሚቆጣጠረው አገር ደላላዎች በተናጠል ወንጀል ለመሥራት አይችሉም። አንድ ተራ ሰው በማግስቱ ሚሊየነር አይሆንም። ከደላላዎቹ ጀርባ ባለሥልጣናት መኖራቸው ግልጽ ነው። የጥቅሙ ዘግናኝነት፣ የሞራል ውድቀቱና የብልግናው መረብ ከአገዛዙና ከባለሥልጣናት ጋር የተያያዘ ነው። ይኼን አደጋ በመመልከትና መፍትሄ እንዲፈለግበት በማሰብ ‹‹ድርጅታዊ ምዝበራ›› የተባለውን መጽሐፌን በኢትዮጵያ እንዲታተም ሞክሬ አልተሳካም። አሁን ላለው ውይይት ይረዳል የሚል እምነት ስላለኝ፣ ታትሞ እንዲሰራጭ ቢደረግ ይጠቅማል።

የችግሩን ጥልቀትና ስፋት በአንክሮ ለሚመለከት ኢትዮጵያዊ ጥገናዊ ሳይሆን መሠረታዊ ለውጥ አስፈላጊ ነው እላለሁ። የባለሞያዎቹ ጥናት እደሚያሳየው ‹‹የስብሰባዎች ወረርሽኝ›› የአገዛዙ መለያ ሆኗል። ለዚህ ብቻ የሚፈሰው ባጀት ትንንሽ ፋብሪካዎች ይሰራ ነበር። ‹‹ወረርሺኙ›› ግልጽነት፣ ተጠሪነትና ኃላፊነት እንዲደበቅ፣ ማን ምን እንደሠራ እንዳይታወቅ፣ ዜጎች በቀጠሮ እንዲጉላሉ፣ ውሳኔ እንዳይደረግ ወዘተ. ሲያደርግ ቆይቷል። ቅልጥፍናን አድክሟል። ኅብረተሰቡ በመንግሥት ላይ ያለውን እምነት በርዞታል። ስለዚህ ነው፣ የደርግ ዓይነት ‹‹ዘመቻ›› እና ግምገማ ስኬታማ ለውጥ ሊያመጣ እይችልም የምለው። ‹‹ዘመቻ›› ቢደረግ በማን ላይ ነው የሚዘመተው? በምን አበይት ጉዳዮች ላይ? ማንን ይለያል? ችግሩ ከከፍተኛ የፓርቲና የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር የተያያዘ ከሆነ፣ ማን በማን ላይ ይዘምታል? ከተዘመተስ በኋላ ውጤቱ ምን ይሆናል? ማን ከሕግ በላይ ሆኖ እንዳይነካ ይደረጋል? በኢሕአዴግ ውስጥ ያሉ አባል ፓርቲዎች በአንድ ድምጽ ሠርተው ማንኛውንም ወንጀለኛ ለፍርድ ለማቅረብ ተዘጋጅተዋል ወይስ አልተዘጋጁም? የዚህ አደጋስ ምንድን ነው? ጥያቄዎቹ መሠረታዊ ለውጥን የሚመለከቱ ናቸው።

መሠረታዊ ለውጥ ስል ማንኛውም የመንግሥት ባለሥልጣን ከሕግ በላይ መሆን የለበትም ማለቴ ነው። እውነተኛ ዴሞክራሳዊ ሥርዓት ለመመሥረት በሩ ክፍት መሆን አለበት ማለቴ ነው። የሕዝብ ተቋሞች፣ ለምሳሌ የማኅበረሰብ ድርጅቶች ነጻ ይሁኑ ማለቴ ነው፣ የመገናኛ ብዙሃን ነጻ ይሁኑ ማለቴ ነው። ያለምንም ማስረጃ የታሰሩ ኢትዮጵያውያን ይለቀቁ ማለቴ ነው። ኪራይ ሰብሳቢነት፣ ጉቦ፣ አድልዎ፣ ሙስናና ከአገር እየተሰረቀ የሚሸሸው ግዙፍ ሀብት ይቁም፣ ቢቻል ይመለስ፣ ወንጀል የፈጸሙት በሕግ ይጠየቁ፣ ሕግ በጉቦ፣ በአድልዎና በወገን ትስስር አይሰራ ማለቴ ነው። ሁሉም የፓርቲ፣ የመንግሥትና ሌሎች ባለሥልጣናት ያላቸውን የግልና የቤተሰብ ገቢና ሀብት መጠንና የሀብቱን የሴክተር ስርጭትና ቦታ ለሕዝብ ይፋ ያድርጉ ማለቴ ነው። በአጭሩ የኢትዮጵያ የአገዛዝ ሥርዓት በቅርቡ ነጻና ፍትሐዊ ምርጫ እንዳካሄደችው እንደ በርማ እንዲሆን አመቻች ሁኔታ ይፈጠር ማለቴ ነው። ፕሬዝደንት ኦባማ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ያነሷቸው እነዚህን የመሳሰሉትን የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን ነበር። የዚህ ዓይነት ሂደት የአመራር ደፋርነትንና ቆራጥነትን ይጠይቃል። ባለሞያዎቹ ያሳዩትን ቆራጥነትና ድፍረት የመንግሥትና የፓርቲ ባለሥልጣናት ቢያሳዩ እመርታዊ ለውጥ የሚመጣበት ድልድይ ይሠራል የሚል እምነት አለኝ።

የኢትዮጵያ የእድገት መርህ ዛሬ ማነቆ ሆኖ ሥራ የመፍጠርና የማምረት ኃይሏን ያገደበው የመንግሥት ወይም የአገዛዝ አድካሚነትና ብልሹነት ነው። ለምሳሌ፣ እጥፍ እድገት አለ በሚባልባት አገር ዐሥራ አምስት ሚሊዮን ሕዝብ እየተራበ ነው። በምግብ ራስን የመቻል ጥረት ስኬታማ ያልሆነበት የፖሊሲ፣ የመዋቅር፣ የቴክኖሎጅ፣ የባህል ወዘተ. ምክንያት ለውይይት መቅረብ አለበት። ሕዝቡ ድምጽ ስለሌለው፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስለተበታተኑ፣ ስለተከፋፈሉ፣ ስለታፈኑ ወዘተ፣ ከመንግሥት ቁጥጥር ነጻ የሆኑ የመገናኛ ተቋሞች ስለሌሉና ነጻ ጋዜጠኞች ስለታሰሩ ወይንም ከአገር ሸሽተው ስለወጡ፣ ሲቪክ ማኅበራት ፈጽሞ ስለፈራረሱ፣ ነጻ የሞያ ድርጅቶች ስለሌሉ የእድገቱ እውነተኛ ገጽታና ውጤት ሊታወቅ አልቻለም። ይኼን የምልበትን ምክንያት ለማጠናከር እፈልጋለሁ። ዓለም ባንክ The Road to 2050: Sustainable Development for the 21st Century በተባለው የታወቁ ባለሞያዎች ባቀረቡት አቅጣጫ አመልካች ጽሁፍ እንዲህ ይላል። ‹‹Governance is a major constraint on development today, and rectifying this will require both institutional reforms, and the mobilization of civil society.›› ከላይ የጠቀስኩት በባለሞያዎቹ የቀረበው ትንተናና ትችት ይኼን አመልካች ጽንሰ ሐሳብ ያንጸባርቃል፣ በኢትዮጵያዊያን መቅረቡ ያስመሰግናል። መልካም አስተዳደር ዘላቂነት ላለውና ፍትሐዊ ለሆነ እድገት ወሳኝ ነው። ከሆነ፣ የፓርቲና የመንግሥት ባለሥልጣናት በሕዝብ ድምጽና በሕዝብ የሥልጣን የበላይነት ማመን አለባቸው። የማኅበረሰቡን ክፍል ማንቀሳቀስ ለዘላቂና ለፍትሐዊ እድገት ወሳኝ ነው ሲባል የሚገባኝ ነጻነት ይኑር፣ ሰብአዊ መብቶች ይከበሩ፣ የሕግ የበላይነት ይኑር ወዘት ማለት ነው። ልማት በዐዋጅና በዘመቻ፣ልማት በማስፈራራት፣ ልማት በኃይል መሠረት ሊይዝ አይችልም። የሕዝብ

> **ለኢትዮጵያ ፈጣን እድገት ከፍተኛ ግብዓት ያደረገው የውጭ እርዳታ ነው። እንደ ዓለም ባንክ ያሉ ለጋስ ድርጅቶችና መንግሥታት ለምን የሚያምኑበትን የአገዛዝ ማነቆነት እንዲፈቱ፤ ራሳቸው ማነቆ እንዳይሆኑ ጫና አያደርጉም? የሚል ጥያቄ አግባብ አለው**

ፈቃደኛነት፣ ተሳትፎ፣ ባለቤትነትና የሚታይ ጥቅም መኖር አለበት። የእርሻን ምርት ለመጨመርና አካባቢን ለመንከባከብ ገበሬው የራሴ ነው የሚለው ሀብት መኖር አለበት። ዓለም ባንክ ካቀረበው የመልካም አገዛዝ አስፈላጊነት ጽንሰ ሐሳብ አከራካሪው ነጥብ እንደሚከተለው ነው።


ለኢትዮጵያ ፈጣን እድገት ከፍተኛ ግብዓት ያደረገው የውጭ እርዳታ ነው። እንደ ዓለም ባንክ ያሉ ለጋስ ድርጅቶችና መንግሥታት ለምን የሚያምኑበትን የአገዛዝ ማነቆነት እንዲፈቱ፣ ራሳቸው ማነቆ እንዳይሆኑ ጫና አያደርጉም? የሚል ጥያቄ አግባብ አለው። በኪራይ ሰብሳቢነት የተበከለ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበረሰብ አገዛዝ ሥር ነቀል የሆነ የበላይነት የሚያካሂደውና የእድገት ጥቅሞችን በአብዛኛው ለጥቂቶች የተሳሰሩ ቡድኖችና ታማኞች የሚያሸጋግረው ብሔራዊ የሆኑ ተቋሞችን ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ነው። ለምሳሌ፣ ጠባብ ጎሰኛነትና ደላላነት አግባብ አለው የሚለው ሂደት ዋጋ ይከፈልበታል። ከገበያ ውድድር ጋር አብሮ አይሄድም። ውድድር በግልጽና ሕጋዊ በሆነ ደንብ የሚካሄድ ጉዳይ ነው። ኪራይ ሰብሳቢነትና ከዚህ ጋር የተያያዘው ደላላነት በግልጽና በሕግ ሊካሄድ አይችልም። ተቋሞች የአንድ ፓርቲ አገልጋይ እስከሆኑ ድረስ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች ሊያገለግሉና ድምጻቸውን ሊሰሙ አይችሉም። ባለሥልጣናቱና ባለሀብቶቹ ተደጋግፈው አሸናፊውን ይመርጣሉ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያሳሰቡት ይኼ እንዳይሆን ነው። ከመንግሥት ቁጥጥር ነጻ የሆኑ የማኅበረሰብና የሞያ ድርጅቶች፣ የመገናኛ ብዙሃን ፍጹም በሆነ ደረጃ ስለወደሙ ወይንም ስለታፈኑ፣ የሕዝብ ድምጽና መብት አብሮ ታፍኗል፣ አብሮ ወድሟል። ክትትል የሚያደርግ ነጻ ተቋም የለም። የዚህ አድካሚ ውጤት በመሬት ይታያል። ተራው ኢትዮጵያዊ በፖሊሲና በባጀት አጠቃቀም ድምጽ እንዳይኖረው አቅቦታል። በጎሳ ልሂቃን የበላይነት የተቀረጹ ተቋሞች የሚያገለግሉት የፈጠራቸውን የበላይ አካል ስለሆነ አንዱ ተቋም ሌላውን ሊገታው ወይም ሊቆጣጠረው አይችልም። ስለዚህ፣ ሁሉን የሚያሳትፍ በጨዋነት የሚመራ ብሔራዊ ውይይት ያስፈልጋል። ይህ አገር አቀፍ ውይይት ተቃዋሚውንና የተገለለውን ክፍል ለማሳተፍ ካልቻለ መሠረታዊ ለውጥ አይቻልም። ጥገናዊ ለውጥ ይቻላል።

አሁን ያለው የአገዛዝ ሁኔታ የሚያሳየው የሚያመዛዝን፣ ፍትሕ የሚሰጥ አካልና የሥልጣን ቁጥጥር የሚባል ነገር እንደሌለ ነው። የሲቪክ ማኅበራት መፋፋት የፖለቲካ ወይም የመንግሥት መልካም አገዛዝ ጥያቄ ነው። በእኔ አመለካከት፣ የኢትዮጵያን እድገት ከማኅበራዊው፣ ከፖለቲካው፣ ከአስተዳደሩ፣ ከነጻነቱና ከሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ለይቶ ለማቅረብ አይቻልም። የአገዛዙ አፈጣጠር፣ አወቃቀርና አሠራር የተሳሰረ፣ የተቆላለፈና የተደጋገፈ ስለሆነ ችግሩም በሥርዓቱ አድካሚነት መነጽር መታየት አለበት እላለሁ።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ መሠረታዊ ችግር የአገዛዝ መጥፎነት ነው። ስግብግብነት፣ በአጭር ጊዜ ማንኛውንም ነገር ሠርቶ መክበር፣ ለአገርና ለወገን አለመቆርቆር ወዘተ. ባህልን የፈጠረው ሥርዓቱ ነው። የአገዛዙ መርህና ተቋሞች ካልተለወጡ ዘላቂነትና ፍትሐዊነት ያለው እድገት የሚቻል አይመስለኝም። ተቋሞች ይለወጡ ስል የሰብአዊ መብቶችና ነጻነት አይታቀቡ፣ የስለላ መረብ ሥር ነቀል በሆነ ደረጃ የአገዛዝ ስልት መሆኑ ይለወጥ፣ የሕወሓትና ተቋሞቹ ሞኖፖሊዎች ይፋ ሆነውና ተወግደው ወይም ተለውጠው የግል የኢኮኖሚ ውድድር እንዲስፋፋ ይደረግ፣ ኪራይ ሰብሳቢነት፣ ድርጅታዊ ምዝበራ፣ ጎሳዊ አድልዎ፣ ጉቦ፣ ሙስና ከአገር ተሰርቆ የሚሸሽ ግዙፍ ሀብት ሕጋዊ ክትትል ይደረግበት ማለቴ ነው። ዓለም ሊክደው የማይችለው ዐቢይ ጉዳይ፣ ‹‹እድገት አለ›› ቢባልም የኢትዮጵያን ሕዝብ ስቃይ የሚያሳዩ መስፈርቶች እየባሱ እንጂ እየተሻሻሉ አለመሄዳቸውን ነው።

የኢትዮጵያን ሁኔታ ከአሜሪካኖች የበለጠ የሚከታተልና የሚያውቅ የለም። የአሜሪካ ‹‹በጎ አድራጊዎች›› ኢትዮጵያን ወረዋታል የሚሉ ብዙ ታዛቢዎች አሉ። እነዚህ ‹‹በጎ አድራጊዎችና ባለሞያዎች›› መልካም አስተዳደርን ፈጽሞ አይነኩትም። የሚያስተናግዱት የራሳቸውንና የሚወክሉትን አገር ጥቅም ነው። የአሜሪካ መንግሥትም ዘገባዎች ከማውጣት ሌላ ጥርስ ያለው ውሳኔ አያደርግም። የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር እ.ኤ.አ.ሰኔ 25 ቀን 2015 ‹‹U.S. Department of State, 2014 Reports on Human Rights Practices›› በሚል ርእስ ያቀረበው ዘገባ የኢትዮጵያን ሕዝብ አሰቃቂ ሁለገብ ሁኔታ ያሳያል። ‹‹The most significant human rights problems included restrictions on freedom of expression, including continued restrictions on print media and on the internet, and restrictions on freedom of association, including through arrests; politically motivated trials; and harassment and intimidation of opposition members and journalists. The government continued restrictions on activities of civil society and nongovernmental organizations (NGOs) imposed by the Charities and Societies Proclamation (the CSO law).››

በእኔ እምነት ሕወሓት/ኢሕአዴግ ተቃዋሚዎቹን ሁሉ የሚቀጣበት የፀረ ሽብርተኝነት ሕግም አብሮ መታየት አለበት። ሁለቱ ሕጎች የሚቃወመውን ግለሰብ ሁሉ መቅጫ መሣሪያ ሆነው ያገለግላሉ። በዚህ መሠረት ገዢው ፓርቲ ለሥልጣኑ ተወዳዳሪ ወይም አስጊ የሆነውን ግለሰብ ሁሉ በፈጠራ መረጃ ከሶ ያስቃያል። በሌላ በኩል ሀብት ያለውና ከገዢው ፓርቲ ባለሥልጣናት ጋር ቁርኝት ያለው ግለሰብ ወህኒ ቤት አይገባም፣ ቢገባም ይለቀቃል፣ ሥራውን ሠርቶና ሀብቱን ይዞ፣ ልጆቹን አስተምሮ ይኖራል። ጠበቃዎች በሞያቸው ከመከራከር ይልቅ ‹‹ዛሬ ይኼን ጉዳይ ማን ይዳኛል›› ብለው ሲጠይቁ ፍርድ በግንኙነትና በጉቦ እንጂ በሕግ አግባብነት የማይተዳደርና የማይስተናገድ መሆኑን ያሳያል።



## ታሪክና ኅብረተሰብ

ታዴዎስ ታንቱ
(የስልክ ቁጥር:- 0934996138 ፣ የመ.ሳ. ቁጥር:- 43414)

# የወቅቱ የሥነ መንግሥት ማኅበራት ስለለፍ

የአገራችን የሥርዓተ አገዛዙ ተቃዋሚዎች ሁሉ አንድ ሆነው ለትግል እንዲነሱ በየወቅቱ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል። አሁንም ሐሳቡን አንግበው የሥነ መንግሥት ማኅበራትን በማግባባት ተግባር የቀጠሉ እንዳሉ ታውቋል። አገርን ለማዳን በቅንነት የሚሰነዘር ሐሳብ ሁሉ በእርግጥ በበጎ ገኑ የሚታይ ይሆናል። በዚህ ላይ ተቃውሞ አናሰማም። ነገር ግን ያለአዋቂዎች ምክር ማንንም የትም ሊያደርስ እንደማይችል ደግሞ ማወቅ አለብን። የአንድነት ሐሳብ አፍላቂ የግል ተነሳሽ በጎ አሳቢ ፈቃደኛ መልዕክተኞች የኢትዮጵያን የሥነ መንግሥት ማኅበራት የኃይል አሰላለፍ ውስጣዊ ይዘትን እንኳን ለይተው የማያውቁ ናቸው። በምክንያቱ ምክንያት ያለ ዕውቀት በሥነ መንግሥት ማኅበራት ላይ ዘምተዋል። ጨለማና ብርሐን እንዴት አንድ ሊሆን ይችላል? እንዴት ሊሆን ይችላል? ተቃዋሚ መሆን አንድ ነገር ነው። የሥነ መንግሥት መርሐ ግብር በይዘት ተመሳሳይ መሆን ሌላ ጉዳይ ነው። ታዲያ ተቃዋሚ መሆናቸውን የተናገሩ ሁሉ እንዴት አንድነት ሊፈጥሩ ይችላሉ? የዓላማ ተመሳሳይነት ሳይኖር የተግባር አንድነት እንዴት ሊመጣ ይችላል? አንድ የሥነ መንግሥት ማኅበር ተቃዋሚ መሆኑን ስለገለጸ ብቻ በተቃዋሚነት ልንመድበው ደግሞ አይገባም። በተግባር የግድ መፈተን አለበትና። በራሱ ጎሳ ስም የአገዛዙን የምርጫ ቦርድ የምስክር ወረቀት የተሸከመ እንዴት ተቃዋሚ ሊሆን ይችላል? የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀንደኛ ጠላት የሆኑ የዛሬዎቹ ገዢዎቻችን ከመነሻው የጎሳ ምልምሎች መሆናቸው ይታወቃል። ታዲያ በጎሳ የተደራጀ የሥነ መንግሥት ማኅበር በምን ሒሳብ ተቃዋሚ ይሆናል? በቅርጻዊ አደረጃጀት ጌታውን መስሎ በይዘት እንዴት ነጻ አውጭ ሊሆን ይችላል? ይህ ማንንም ሊያሳም የማይችል አቅመ ቢስ ተጠየቅ ነው።

ስለእውነት በእውነት እንነጋገር። አንድ የሥነ መንግሥት ማኅበር ከገዥው ወገን በተቃራኒ አቋም ለመገኘቱ መገለጫው ተግባር ነው። ወሬ አይደለም። የሥነ መንግሥት ማኅበራት ከሕዝብ ድጋፍ ለማገኘት ሲሉ ተቃዋሚ መሆናቸውን ሊናገሩ ይችላሉ። መቀበል ግን የለብንም። ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር ተቃዋሚ መሆናቸውን የሚናገሩ በጣም ብዙ የሥነ መንግሥት ማኅበራት አሉ። እውን እነዚህ የሥነ መንግሥት ማኅበራት ተቃዋሚ ናቸውን? በፍጹም አይደሉም። ተቃዋሚ ለመባል በገዢው የሥነ መንግሥት ማኅበርና በተቃራኒው መካከል መሠረታዊ ልዩነት ሊስተዋል ይገባል። ሕይወት ያለው ተጨባጭ ልዩነት በሁለቱ መካከል በግልጽ መታየት አለበት። ማስመሰል አይቻልም። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ተቃዋሚዎች መሆናቸውን ከሚናገሩ የሥነ መንግሥት ማኅበራት አብዛኞዎቹ የሥርዓተ አገዛዙ የእጅ ሥራዎች ናቸው። ጸረ አንድነት ናቸው። ጸረ ኢትዮጵያ ናቸው። ጸረ ሕዝብ ናቸው። ለሥነ መንግሥታዊ ዓላማ በጎሳ መደራጀት በራሱ ወንጀል ነው። ገዥዎቻችን በጎሳ ተደራጅተዋል። ወንጀለኞች ናቸው። ለወንጀል ዓላማ ተደራጅተዋል። ለዓመታት ወንጀል ሠርተዋል። አሁንም ወንጀል ሲሠሩ ይስተዋላል። በወንጀል በልጽገዋል። በወንጀል ከብረዋል። ወንጀልን ከገዥዎቻችን ገዥዎቻችንን ከወንጀል ነጥሎ ማዬት አይቻልም። ገዥዎቻችን በግፍ እንጀራ በልተዋል። በልተዋል! በልተዋል! በልተዋል! ግን ከስተዋል። አሁን ደግሞ አቅመ ቢስ የጎሳ ምልምል የሥነ መንግሥት ማኅበራት በተስፋ ቆመዋል። በገዢው የጎሳ ስብስብ ሥነ መንግሥት ማኅበር ላይ ተለጥፌው ሕዝብን በማታለል ተሰማርተዋል። እውነተኛ ኢትዮጵያውያን ለጎሳ ምልምል ሥነ መንግሥት ማኅበራት በምንም ዓይነት ክብር አንሰጥ! ክብርም አይገባቸውም። በዓላማ ያልተደራጀ የሥነ መንግሥት ማኅበር ሁሉ ጸረ ኢትዮጵያ ነው። መደራጀት መብት ነው። ገዥዎች አይሰጡንም። ገዥዎች አይነሱንም። ዜጎች መብታችንን ለገዢዎች አሳልፈን መስጠት የለብንም። የመደራጀት መብት አለን። የመሰባሰብ መብት አለን። ለአገዛዙ ያለመታዘዝ መብት አለን። ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መበት አለን። ባለመብት ነን!! ነገር ግን በጸረ ኢትዮጵያ አቋም መደራጀት አይበረታታም።

ዛሬ የገዥዎቻችን የኪስ መሀረብ የሆኑ የጎሳ የሥነ መንግሥት ማኅበራት ያለጥርጥር የጥፋት ተልዕኮ አንግበዋል። በኢትዮጵያ የአስተዳደር በደል ያልደረሰበት ማንም የለም። ይህ ምንን ያመለክታል? ይህ በአገራችን ለዘመናት የመደብ ጭቆና መኖሩን ያሳየናል። በደርግ አስተዳደር በእርግጥ የመደብ ጭቆናው ተወግዷል። ነገር ግን አሁንም ተመልሶ መጥቷል። በኢትዮጵያ በእርግጠኝነት አሁን የዘር ጭቆና አለ። ከአንድ ጎሳ በስተቀር የተቀሩት ሁሉ ተጨቁነዋል። በተጓዳኝም የመደብ ጭቆና አለ። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ድርብ ጭቆና አለበት። ቀዳሚው የዘር ጭቆና ነው። በግልጽ ይታያል። አንድ ዘር ብቻውን የኢትዮጵያን የሥነ መንግሥት ሥልጣንና ብሔራዊ ሀብት ሰብስቦ ይዞታል። ይህ ምን ማለት ነው? አንድ ጎሳ የተቀሩትን የኢትዮጵያ ጎሳዎች ሁሉ ረግጦ ባሪያ አድርጎ ይገዛል ማለት ነው። የመደብ ልዩነት ደግሞ ከተገኘ ጎሳዎች በተመለመሉ ሹማምንት በሰፊው ሕዝብ መካከል ይስተዋላል። በዚህ ምክንያት በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የዘርና የመደብ ጭቆና በግልጽ ይታያል። በትናንትናዪቱ ኢትዮጵያ ግን የዘር ጭቆና አልነበረም። የመደብ ጭቆና ብቻ ነበረ።

> ዜጎች በኢትዮጵያ ምድር በየትም ቦታ ሳይሸማቀቁ የሚኖሩበትን ሥርዓተ አስተዳደር መዘርጋት አለብን። ኢትዮጵያን የሁላችን የሚያደርግ አስተዳደር እንሻለን።

ያም ሆነ ይህ ሰው በላውን ገዥውን የጎሳ ሥነ መንግሥት ማኅበር ከሥልጣን ለማስወገድ በተመሳሳይ መልኩ በጎሳ መደራጀት አላዋቂነት ነው። ወይም ክሕደት ነው። ጠላትህን ለማሸነፍ ጠላትህ በሄደበት መንገድ እንዴት ትሄዳለህ? በቅድሚያ የአንተ ጠላት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ጠላት መሆኑን ማወቅ አለብህ። ገዢዎቻችን ጠላቶቻችን መሆናቸውን እንወቅ። እስቲ ልጠይቅ! ኢትዮጵያዊ ነህ ወይስ አይደለህም? ኢትዮጵያዊ ከሆንህ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ለምን በዓላማ አልተደራጀህም? ኢትዮጵያዊ ካልሆንህ ደግሞ የረገጥከው መሬት የኢትዮጵያ ሕዝብ በመሆኑ ጥለህ ሒድ! የግልህ የሆነ መንደር፣ ወረዳ፣ አውራጃ፣ ክፍለ አገር ወይም ክልል ፈጽሞ የለህም። ገዥዎቻችን ለጊዜው ኃይል እንደተሰማቸው ይገባናል። ነገር ግን የግላቸው የሆነ አንድ ስንዝር መሬት እንኳ የላቸውም። ለአገር ደምተው፣ ቆስለው ወይም ሞተው አያውቁምና። በኮሎኒያሊስት ኢጣሊያ ወረራ ወቅትም ሆነ ፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በመጣ ጊዜ በአድዋ፣ በተንቤን፣ በሽሬ፣ በአምበራዶም፣ በመቀሌ፣ በማይጨው እንዲሁም በሌሎችም የትግራይ መሬቶች እንደ ቅጠል የረገፉት ከምሥራቅ፣ ከምዕራብና ከመሀል ኢትዮጵያ ወደ ሰሜን የዘመቱ ውድ የኢትዮጵያ ጀግኖች መሆናቸውን ሊያውቁት ይገባል። የነጻነት ትርጉም በቃላት ሳይሆን በተግባር ያስተማረውን ሕዝብ ዛሬ የባንዳ ልጆች ረግጠው ሲገዙት ከማዬት በላይ የሚያቃጥል ምን ነገር አለ?

ተወደደም ተጠላም በአሁኑ ወቅት በዘር መደራጀት ጠባብ ምኞቱን ከግብ ለማድረስ የሚቅበዘበዝ የጎሳ ሥነ መንግሥት አራማጅ ሁሉ በአቋም የሕዝብና የአገር ጠላት ከሆኑ ገዥዎቻችን ጋር ይመደባል። እንደገዥው ጎሳ አቅም እንደሌለው ይገባናል። በኢትዮጵያ ሥነ መንግሥትና ብሔራዊ ሀብት ላይ የሰናፍጭ ቅንጣት ታክል ተጽዕኖ ለማድረግ የሚችል የጎሳ ሥነ መንግሥት ማኅበር አለመኖሩን በእርግጥ እንረዳለን። ዘወትር የአገዛዙን ኮንትራት ለማደስ የጎሳ ሥነ መንግሥት ማኅበራት በየአምስት ዓመቱ ከመንቀሳቀስ ያለፈ ታሪክም የላቸውም። የጎሳ ሥነ መንግሥት ማኅበር በዓለም ታሪክ የተተፋ ነው። ቦታም የለውም። እንደ ሥነ መንግሥት ማኅበር ፈጽሞ አይታይም። የኢትዮጵያ ሕዝብም አክ እንትፍ ሊለው ይገባል። አንድ ዶክተር ወይም ፕሮፌሰር ተብየው የባንዳ ገዥዎቻችን ትእዛዝ ተቀብሎ የጎሳ ሥነ መንግሥት ማኅበር እንዴት ይመሠርታል? በጣም ያሳፍራል። ምሁር እንዴት የገዥዎችን ትእዛዝ እንደወረደ ይቀበላል? የእርሱ ምሁርነት ተመራቂ ተማሪዎችን ለማማከር ብቻ ነው እንዴ? አእምሮው ስለወደፊት የኢትዮጵያ እጣ ፈንታ ትንሽ እንኳ አያስብም? ለመጭው ትውልድ መከፋፈልንና መለያየትን እንደሚያስተምር ማሰብ እንዴት ተሳነው? ዶክተር የተባለው በኢንተርኔት በመጣ ዲግሪ ነው እንዴ? ፕሮፌሰር የተባለው አንዳችም ምርምር ሥራ ሳይሠራ ለአለቆቹ የሰላምታ ደብዳቤ በመጻፍ ሳይሆን አይቀርም።

ገዥዎቻችን ከበረሃ ከወጡ አንስቶ ዲፕሎማና ዲግሪ በኢንተርኔት እንዲሁም በፖስታ ቤት በኩል ይጎርፍላቸዋል። ይህን እናውቃለን። ነገር ግን ቀደም ሲል የዓለም አቀፍ መመዘኛዎችን አሟልተው ከሙሉ ክብር ጋራ አካዳሚያዊ ብቃታቸው የተመሰከረላቸው ምሁራን እንዴት ወደገዥዎቻችን ደረጃ ወረዱ? እነዚህ ምሁራን ያለጥርጥር ተንቀሳቃሽ አስከሬን ሆነዋል። ለዚህም ቆም ብለው ሊያስቡ ይገባል። ያስተማረቻቸው ኢትዮጵያ እናታቸው መሆኗን ያስታውሱ። አያት ቅደመ አያቶቻቸው ከከብት ጭራ ለአፍታ እንኳን ሳይለዩ መሞታቸውንም ማስታወስ ይጠበቅባቸዋል። በተሻለ ዘመን ላይ መድረስ የተሻለ ለመሥራት እንጂ ለጥፋት ሊሆን አይገባም። አሁንም እንላለን። መደራጀት መብት ነው። በጎሳ መደራጀት ግን ጥፋት ነው። የፈለጉትን ርዕዮተ ዓለም በማንገብ ዘር፣ ቋንቋ፣ ባህልና ሃይማኖት ከግንዛቤ ሳይገቡ በዓላማ ብቻ በመደራጀት የሥነ መንግሥት ሥልጣንን ለመጨበጥ መታገል መብት ነው። ማንም በሕዝብ ከተመረጠ ኢትዮጵያን ሊመራ ይችላል። አገር የጋራ ናትና። ይህን ልናውቅ ይገባል። በጎሳ መደራጀት ክህደት ነው። ባንዳነት ነው።

በሁለተኛ ደረጃ ከጎሳ የሥነ መንግሥት ማኅበራት ባላነሰ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል የጎዱት ደግሞ በገዥው ሥነ መንግሥት ማኅበር ላይ የተለጠፉ አገር አቀፍ የሥነ መንግሥት ማኅበራት ናቸው። እነዚህ የሥነ መንግሥት ማኅበራት በገዥዎቻችንና በሕዝቡ መካከል የማይታረቅ ቅራኔ መኖሩን አያምኑም። የሥነ መንግሥት ዕውቀት ይጎድላቸዋል። ትግሉ የነጻነት መሆኑን አይቀበሉም። ዘወትር ሥልጣንን በጉርሻ መልክ ሲቋምጡ ኖረዋል። እነዚህ በአቋም የሞቱ ልጥፍ የሥነ መንግሥት ማኅበራት ለገዥው የሥነ መንግሥት ማኅበር ሳያቅማሙ ሲታዘዙ ይስተዋላል። መሠረታዊ ለውጥ አይሹም። በገዥው ሥነ መንግሥት ማኅበር ላይ ተለጥፈዋል። ከፍርሃት የተነሳ በቁማቸው ሞተዋል። ትግል አይወዱም። የምርጫ ወቅት ሲደርስ ለምርጫ ቦርድ ይላላካሉ። ሥልጣንን ይቋምጣሉ። ሆዳቸውን ማዕከል አድርገው ይንቀሳቀሳሉ። ከምርጫ በኋላ አፋቸው ዘግተው ይጠፋሉ። እነዚህ በቁማቸው የሞቱ የሥነ መንግሥት ማኅበራት አሁን ዝም ብለው ተኝተዋል። ምርጫ ሲደርስ ደግሞ የሚንቀሳቀሱ ይሆናል።

ትግል የማያቋርጥ ሂደት ነው። እውነተኛ ለሕዝብ የቆመ የሥነ መንግሥት ማኅበር ሕዝቡ ነጻ ሳይወጣ ትግሉን አያቋርጥም። ልጥፎቹ የሥነ መንግሥት ማኅበራት ግን ይህን አያስቡም። ነጻነትን አያስቡም። ምርጫ በደረሰ ጊዜ ልጥፎቹ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ገዥዎች ሥልጣንን እንዲሰጧቸው ይቋምጣሉ። ግን አያገኙም። እንዳማራቸው ይቀራሉ። ደግሞ ሌላ የምርጫ ዘመን ይጠብቃሉ። እንደ አሜሪካና አውሮጳ አገራት የሥልጣን ሽግግር ይጠብቃሉ። የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ አያውቁም። አይገባቸውም። በበለጸጉ አገሮች በእርግጥ የሥልጣን ሽግግር ብቻ ይሆናል። ሰው ሰውን ሳይሆን ሕግ ሰውን በሚገዛበት አገር በእርግጥ የሥልጣን ሽግግር ይደረጋል። በቃ! ሌላ የሚያስፈልግ ነገር የለም። በምርጫ የሥልጣን ቅብብሎሽ ይፈጸማል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ግን የሥነ መንግሥት ተልዕኮ ሌላ ይሆናል። መሠረታዊ ለውጥ ይጠይቃል። ኢትዮጵያ አንዳችም ሥነ መንግሥታዊ፣ ሕጋዊና ታሪካዊ መብት የሌላቸው ጎርፍ አመጣሽ የአንድ መንደር ምልምሎች የሚጫወቱባት አገር ናት። ኃላፊነት የማይሰማቸውና ተጠያቂነት የሌላቸው የትናንት ሹምባሾች የዛሬዎቹ ቄሳሮች ወርቅ የሚዝቁባት አገር ከሆነች ዓመታት ተቆጥረዋል። ታዲያ በዚህ ሁኔታ የሥልጣን ሽግግር ማለት እኮ አሁን የባንዳ ልጆች ጨምድደው የያዙትን ሥነ መንግሥታዊ ሥልጣን ለሌሎች ባንዳዎች ማስተላለፍ ማለት ነው። ይህ ደግሞ እነርሱ ራሳቸው መተካካት ከሚሉት ጋር ይመሳሰላል። ለዚህ ትግልም አያስፈልግም። ጊዜውን ጠብቆ ይመጣል። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እውነተኛ ነጻነት ያስፈልገዋል። ለውጥ ያስፈልገናል። መሠረታዊ ለውጥ የግድ ይላል። አሁን የሚገዙን ወንጀለኞች በፍርድ አደባባይ መቆም አለባቸው።

ዜጎች በኢትዮጵያ ምድር በየትም ቦታ ሳይሸማቀቁ የሚኖሩበትን ሥርዓተ አስተዳደር መዘርጋት አለብን። ኢትዮጵያን የሁላችን የሚያደርግ አስተዳደር እንሻለን። የኢትዮጵያ አንድነት ተጠብቆ ለትውልድ የሚቆይበት ሥርዓተ አስተዳደር ለማምጣት እንታገል። የጎሳ ሥነ መንግሥት ማኅበራትን በተግባር አክ እንትፍ እንበላቸው። የፊደል ምሁራንን አንከተላቸው። ቦታ እናሳጣቸው። ተለጣፊ አገር አቀፍ ሥነ መንግሥት ማኅበራትንም ቀስ በቀስ የራሳቸውን ሞት እንዲሞቱ እናድርጋቸው። ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር ምርጫ ቦርድ ከተባለው አካል የምስክር ወረቀት ተቀብለው የሥነ መንግሥት ትግል ከሚያካሂዱ መካከል አንድ ወይም ሁለት የሥነ መንግሥት ማኅበራት ብቻ አገርን ማዕከል አድርገው ሲንቀሳቀሱ ይስተዋላል። ሌላ ማንም የለም። የተቀሩት ሁሉ በአሰላለፍ ከገዥው የሥነ መንግሥት ማኅበር ጋር ቆመዋል። ለኢትዮጵያ ሕዝብ አይጠቅሙም። ለነጻነት ትግላችን የሚያበረክቱት አንዳችም አስተዋጽኦ የለምና።

በመቀጠል ደግሞ በትጥቅ ትግል የተሰማሩ የሥነ መንግሥት ማኅበራት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ግንዛቤ ሊጨበጥ ይገባል። ከመካከላቸው በአሁኑ ወቅት ኦብነግና ኦነግ በአገር ውስጥ ለገዥዎቻችን የጎሮሮ አጥንት ሆነዋል። ገዥዎቻችን ሁለቱንም በአሸባሪነት መድቧቸዋል። የማስመሰል ችሎታ አላቸውና። ገዥዎቻችን ራሳቸውን ከማሻገር በላይ የከፋ ወንጀል ሲሠሩ ይስተዋላል። በሕግ አይጠየቁም። በውል እናውቃለን። ሥልጣን ላይ ከመውጣታቸው በፊት ገዥዎቻችን ከኦነግና ከኦብነግ ጋር አንድ ላይ ሠርተዋል። ኢትዮጵያን ለመበታተን የሚተጋ ሁሉ ለገዥዎቻችን የልብ ወዳጅ ይሆናል። ይህን አሳምረን እናውቃለን። ገዥዎቻችን ሊያታልሉን አይችሉም። እናውቃቸዋለን። ነገ ከሥልጣን የሚያስወግዳቸው ኃይል ሲመጣ ሳያቅማሙ ከኦነግና አብነግ ጋር እንደሚሰለፉ ለመናር ነብይ መሆን አያስፈልገንም። ጠላት ምንጊዜም ወዳጅ አይሆንም። ገዢዎቻችን በምንም መንገድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጅ ሊሆኑ አይችሉም። ለጥፋት የመጡ ናቸውና። ኢትዮጵያዊም አይደሉም። በእምቅ አገላለጽ ኦብነግ፣ ኦነግ፣ የገዥዎቻችን የሥነ መንግሥት ማኅበር፣ የጎሳ የሥነ መንግሥት ድርጅቶችና ተለጣፊ አገር አቀፍ የሥነ መንግሥት ማኅበራት ሁሉ በኃይል አሰላለፍ በጥፋት ጎራ ቆመዋል። በተቃራኒ ጎራ ደግሞ አንድ ወይም ሁለት አገር አቀፍ የሥነ መንግሥት ማኅበራት ብቻ ለነጻነት ሲታገሉ ይስተዋላል። ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ይህን ይመስላል። በዚህ ምክንያት የነጻነትና የአንድነት ኃይሎችን የሚያበረታታ ሁኔታ አናይም። ተስፋም አንቆርጥም። ገዥዎቻችን ከጫንቃችን የሚወርዱበት ቀን ይመጣል።

ገዥዎቻችን ከሥልጣን ከወረዱ ምን እንደሚጠብቃቸው አውቀዋል። ወንጀለኛ ሳያሳድዱት ይሮጣልና። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥነ መንግሥት ንቃተ ሕሊናውን ለማሳደግ ተግቶ ሊሠራ ይገባል። የወገን ጎራ መጠንከር አለበት። በዘር፣ በቋንቋ፣ በጎሳና በቀለም የከፋፈሉንን ከጫንቃችን ለማስወገድ ተግተን እንሥራ። ገዥዎቻችን አንዴም እውነት ተናግረው አያውቁም። በሐሰት የተካኑ ናቸው። በሥልጣን ላይ ለመቆየት ዛሬ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። በዘረፋ ከብረዋል። በዘር ተባድነው የኢትዮጵያን ሕዝብ መሬት ተከፋፍለዋል። ይህን ሞኝ ሕዝብ ውሸት እየመገቡ ለመቶ ዓመታት ለመግዛት ወስነዋል። ምኞታቸው እንዲመክን ለማድረግ በአንድነት እንታገል። አሁን ያለው የጠላትና የወገን አሰላለፍ ሚዛኑ መለወጥ አለበት። የአንድነትና የነጻነት ኃይሎች ትግላችንን በድል ለማጠናቀቅ እንቁረጥ። ሕዝብ ያሸንፋል!!

# ቤንሲያ
## ሲቲፒ ማተሚያ ቤት
## ከኮምፒዩተር ወደ ፕሌት (CTP)

ቤንሲያ ሲቲፒ ማተሚያ ቤት ለህትመት ስራ እጅግ ጠቃሚና በጥራቱ አስተማማኝ የሆነውን ከኮምፒውተር ወደ ፕሌት ህትመት ስራ ከጀመረ እነሆ አንድ አመት ሞላው ። በአለፉት አንድ አመታት ውስጥ ያፈራናቸ ደንበኞቻችን ለኛ ምስክሮቻችን ናቸው።
በዋነኛነት ከምንለይባቸው መካከል ጥራት ፍጥነት ቅልጥፍና ታማኝነት እና የደንበኛ አክብሮት ናቸው ከዚህም ሌላ ማሽናችን ዘመኑ የደረሰበት የቅርብ ግዜ ቴክኖሎጂ ከመሆኑም በላይ የማተም አቅሙም በሰአት እንደሚከተለው ነው።

| የፕሌት ዓይንነት | መጠን | በሰአት የማተም አቅም |
|---|---|---|
| ጂቲኦ 46 | 40 x 38 | 60 |
| ጂቲኦ 52 | 52 x 40 | 60 |
| ኤም ኦ / ኮርድ | 55 x 65 | 50 |
| ስፒድ ማስቴር 74 / ኮርስ | 76 x 62.5 | 45 |
| ስፒድ ማስቴር A1 | 1040 x 840 | 40 |

### ጥራት ቅልጥፍና ታማኝነት እና ታታሪነት የኛ መለያዎች ናቸው !

አድራሻችን ቸርችል መንገድ ቴዎድሮስ አደባባይ (ፒያሳ)
እሸቱ ማሞ ህንፃ አንደኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 113
Tel 09 11 42 12 80
E-mail bbekele@gmail.com
bencia.printing@gmail.com



# አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ
## በሁሉም መጽሐፍት መደብር ያገኙታል

## ትግል አይቆምም



ዮሴፍ ያዘው (ሻለቃ)



# መንቶቾ የዕጽዋት (የባህል) መድኃኒት ማምረቻና መሸጫ
## MENTOCHE HERBAL MEDICINE PRODUCTION CENTER



ይህ የዕጽዋት መድኃኒት ማዕከል ሲወርድ ሲዋረድ የነበረውን የአባቶች የባህል (እጽዋት) መድኃኒት ሕክምና በማሳደግ ፍቱንነታቸዉ ተረጋግጦ በከፊል በሳይንስና ቴክኖሎጅ በማስመዝገብና ከኢንቨስትመንት ፈቃድ በመውሰድ በማምረት ላይ ይገኛል። ለዉስጥ ችግር በሚወሰድ፣ በቆዳ ላይ ለሚወጣ በመቀባት ሲሆን ከኬሚካልም ሆነ ከባዕድ ነገሮች ነጻ የሆነ ነው። ከሚመረቱት ምርቶች በከፊል

### በሚወሰድ
- ለኪንታሮት ፌስቱላ መድሀኒት በደም ዉስጥ ያለን አጥቦ የሚያወጣ ሲሆን ድርቀት፣ ወገብ ችግር፣ ጋዝና ወሲብ ችግርን ያድናል።
- ለነቀርሳ (ካንሰር) በሽታ ከደም ውስጥ አጥቦ የሚያወጣ በጭንቅላት፣ በአንገት፣ በጡትም ሆነ በአንጀት ላይ ያለዉን ያድናል።
- የደም ግፊት (ብዛት) እስከ መጨረሻዉ የሚያድን። የኮሌስትሮል፣ የስብና የፕሮቲን ክምችትን ያቀልጣል፤ ስለሆንም ኮሌስትሮል ያጠፋል።
- ለነርቭ፣ ለሪህ፣ ለደም መወፈር (መርጋት) ለዲስክ መንሸራተት ያድናል።
- ለጉበት ሄፓታይተስ ሦስቱንም አይነት የጉበት በሽታ ያድናል።
- ለአእምሮ ጭንቀት ለሚጥል በሽታና ለሚያፈዘዉ ያድናል።
- ለቆዳ በሽታ አለርጅክም ሆነ ፈንገስ ሶራይስስ ጭምር ያድናል።
- ኤድስን የሚያባብሱ ተዛማጅ በሽታዎችን በማከም የድካም ስሜትን፣ መክሳትንና የምግብ ፍላጎት መቀነስን እንዲጨምር ያደርጋል።
- በሆድ ዉስጥ ላለ በሽታ አሜባ፣ ታይፎይድ፣ ጃርዲያ፣ አስካሪስና ውሃ ወለድ በሽታዎችን ያድናል።
- ‹‹ሸንት ለሚያስቸግረውና ለስኳ በሽታ ፍቱን መድኃኒት አለን››

### የሚቀባና በፊንጣጣ የሚገባ መድኃኒት
- ለኪንታሮት (ፌስቱላ) በሚቀባ ምንም አይነት ህመም የሌለዉ ሲሆን ሥራም የማያስፈታ ነዉ። ለቆየ የአባላዘር ለዉስጥ ኪንታሮት በፊንጠጣ የሚገባ የዉስጥን የፈንገስ ክምችት የሚያወጣ ምንም አይነት የህመም ስሜት የሌለዉ ነዉ።
- ለቆዳ በሽታ ሁሉንም አይነት ያድናል
- ያለ እድሜ ለሚመጣ የወሲብ (የብልት መፍጠን) ችግር በመቀባት የሚያድን አብዛኛዉ ሕዝብ የኪንታሮት በሽታ መድሀኒት በተመጣጣኝ ዋጋ እንሸጣለን።

በተጨማሪም በመገናኛ ውልና ማስረጃ ፊት ለፊት ገነት ኮሜርሻል ሴንተር 2ኛ ፎቅ የመድኃኒት መሸጫና ነጻ የመርጃ ማዕከል መክፈታችን ስናበስርዎ በደስታ ነው።
አድራሻ: አዲስ አበባ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ሃና ማርያም ከጤና ጣቢያው አለፍ ብሎ
0911 665321/ 0913 316790 / 0912 660886 / 011 4710024
ቁጥር 2: ሰሜን ሸዋ መሀል ሜዳ ወርልድ ቪዥን ፊት ለፊት/ ቁጥር 3: ጎጃም በረንዳ እናት ባንክ ካለበት ሕንጻ ላይ 2ኛ ፎቅ 241 ቁጥር